# የነውር እሳቤ በሰሜን አቸፈር ማኅበረሰብ የዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ


ሙሉፀሐይ ገነት [1]

የኔዓለም አረዶ [2]

ዓለሙ ካሣዬ [3]


## አጠቃሎ


ጥናቱ በዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ የማኅበረሰቡን የነውር እሳቤ መተንተንን አላማው ያደረገ ሲሆን ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ነው። በሰሜን አቸፈር ወረዳ ከሚገኙ ሠላሳ ኹለት ቀበሌዎች መካከል በዓላማተኮር ንሞና ስምንት ቀበሌዎችን በመምረጥ በተሳትፏዊና ተዓቅቧዊ ምልከታ፣ በከፊል ነጻና በነጻ ቃለመጠይቅ እንዲሁም በቡድን ተኮር ውይይት መረጃዎች ተሰብስበዋል። መረጃዎቹ በማኅበራዊ ግንባታና በመዋቅራዊ ጠቀሜታዊነት ንድፈሃሳቦች ተቃኝተው ተተንትነዋል። ከግኝቱም በማኅበረሰቡ የዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ የሚስተዋሉ የነውር እሳቤዎች መነሻቸው የማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነቶች እንደሆኑ ከመረጃዎች ታውቋል። ይኸም ማኅበረሰቡ ነውሮችን በመጠበቁ አገኛለሁ ብሎ ከሚያምነውና በአንጻሩ በመጣሱ ደግሞ ይደርስብኛል ብሎ ከሚያምነው ነገር አንጻር የሚታዩ ናቸው። በዕደጥበባቱ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ ከክብር ጋር የተያያዙ፣ ከበረከትና ከገድ ጋር የተያያዙ እንዲሁም ከክፉ ዐይን ተጋላጭነት ጋር የተያያዙ የነውር እሳቤዎች እንዳሉ መረጃዎች አመላክተዋል። በተጨማሪም በማኅበረሰቡ እምነት መሠረት ነውሮች ለተጠኚው ማኅበረሰብ ማኅበራዊና ሥነልቦናዊ መረጋጋት የመፍጠርና መዋቅራዊ ሥሪትን የማጽናት ሚና እንዳላቸው ይታመናል። በአንጻሩ ማኅበረሰቡ ነውር ብሎ ያወጃቸውን ክልከላዎች መጣስ ማኅበረ ባህላዊ ቅጣት የሚያስከትል ሲሆን ቅጣቱም ከክብር መውረድ፣ ትችት፣ ለመጥፎ ነገሮች ተላልፎ መሰጠት፣ የትዳር ፍቺና የማዕረግ ወይም የሹመት መነጠቅ የሚያስከትል እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል።



ቁልፍ ቃላት [ነውር፣ ዕደጥበባት፣ ሰሜን አቸፈር፣ ዐውድ]



[1] በደ/ብርሃን ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል መምህርት Email genetmulutsehay@gmail.com

[2] በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል መምህርት፣ በቁሳዊ ባህል ረዳት ፕሮፌሰር Email yenealem2006@yahoo.ca

[3] በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል መምህር፣ በህገረሰባዊ ልማድ ረዳት ፕሮፌሰር Email alemukas@gmail.com

## 1. መግቢያ

ቁሳዊ ባህል የሰዎችን አዕምሯዊ ሥሪት፣ አመለካከት፣ የሚኖሩበትን ዓለም መዋቅራዊ ሥሪት ለመረዳት የሚያስችል እንደሆነ በመጥቀስ ተጨባጭ ያልሆኑ ወይም የማይዳሰሱ እሴቶች ላይ ለመድረስ ተጨባጭ የሆኑ ወይም የሚዳሰሱ ቁሶችን ማጥናት፣ መተንተንና መተርጎም አስፈላጊ ነው (Glassie1999፡41)። ከዚህ ጋር በተያያዘ Attfield (2000) ቁስ ሲባል በቁሱና በባለቤቱ መካከል ያለው ግንኙነት የሚገለጽበት እና ማኅበረሰቡ ስለማንነቱ የሚያስረዳበት፣ ለሕይወትና ሞት የሚያቀርበውን ትርጓሜ የሚነግርበት እንደሆነ ይገልፃሉ። በመሆኑም የቁሳዊ ባህል ጥናት ቁሱን ብቻ ሳይሆን ሰዎች በቁሱ አማካኝነት የዓለም ዕይታቸውን እንዴት ገለጹ? ባህላዊ ውክልናው ምንድን ነው? እንዲሁም ለማኅበራዊ ግንኙነት እንዴት ማሳያ ይሆናሉ? የሚሉትን ማመላከትንም እንደሚጨምር Attfield (2000) ገልጸዋል።

ቁሳዊ ባህል ሲጠና ከቁሶች አዘገጃጀት ዕውቀት ባለፈ ከዝግጅቱና አጠቃቀሙ ጋር በተያያዘ ያለውን ማኅበረሰባዊ እምነት መመልከት/ማጥናት በቁሱና በማኅበረሰቡ መካከል ያለውን ቁርኝት የበለጠ ለማወቅ ይረዳል። ይህን ለማድረግ የነውር እሳቤዎችና ክልከላዎችን ማጥናት አስፈላጊ እንደሚሆን (Arnoldi 1996፡36-41) እንዲሁም (Donald and Hurcombe, 2000፡ xxi) ገልጸዋል። አያይዘውም በቁሳዊ ባህል ወይም በዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት አሳታፊና አሳታፊ ያልሆኑ ሥርዓተ ፆታዊ ፈቃዶችና ክልከላዎች፣ የአጠቃቀምና የሙያ ለመዳ ሂደትን በተመለከተ የሚታዩ የነውር እሳቤዎች እንዲሁም ወቅትንና ሁኔታን መሠረት ያደረጉ የዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ማኅበረባህላዊ ገደቦች እንዳሉ ይገልጻሉ። ይህ በምሁራኑ የቀረበው ሃሳብም ሥርዓተ ፆታ ተኮር፣ ወቅትና ሁኔታ ተኮር የዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ፈቃድና ክልከላ ለምን ሊኖር እንደቻለ ጥያቄን ይፈጥራል። ይኸውም ቁሶች የእለት ከእለት ተግባርን ከመፈፀሚያነት ባለፈ ልዩ ማኅበረባህላዊ እሴት ተሸካሚዎች እንደሆኑ የሚጠቁም ሲሆን ይህ ሁነትም ዕደጥበባትን ከተራ ቁስነታቸው ወይም ከተቀዳሚ አገልግሎታቸው ባለፈ በልዩ ዕይታ እንዲጠኑ የሚያደርጋቸው ጉዳይ ነው። በመሆኑም በሀገረሰባዊ ዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ ማኅበረሰቡ ዕደጥበባቱን በማን፣ ለምን፣ መቼ፣ እንዴት፣ እንዲዘጋጁና አገልግሎት እንዲሰጡ እንደሚፈቅድ ወይም እንደሚከለክል ለማወቅ የነውር እሳቤዎችን ማጥናት ሁነኛ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ይህ መጣጥፍ በሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ የዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ ያለው የነውር እሳቤ ምን እንደሚመስል ይመረምራል።

ይህ ጥናት በተጠቀሰው ርዕሰ ጉዳይ ላይ የመካሄዱን አግባብነት ለማመላከትና ከቀደምት መሰል ጥናቶች በተለየ ያተኮረበትን የጥናት አቅጣጫ ለመለየት ብሎም ክፍተቶችን ለመሙላት ይረዳ ዘንድ የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ ተካሂዷል። በመሆኑም በተደረገው ዳሰሳ በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር አጥኚዎች የተሠሩ አምስት ጥናቶችን ለማየት ተሞክሯል። ከእነዚህ መካከልም ኹለቱ የምግብ ነውሮች ላይ ሲያተኩሩ የመጀመሪያው በ Hadush et al. (2022) Food taboos and their perceived reasons among pregnant women in Ethiopia: systematic Review በሚል ርዕስ ከተሰሩ 82 ጥናቶች መካከል ለዳሰሳው ብቁ ሆነው የተገኙ 13 ቀደምት መጣጥፎችን

በመዳሰስ የተካሄደ ነው። በጥናቱ በእርግዝና ወቅት የሚከለከሉ ምግቦችን በመጠቆም ምክንያታቸውን አመላክቷል። በግኝቱም በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ማኅበረሰቦች ባህል ውስጥ አንዳንድ ምግቦች ለነፍሰጡር ነውር ተደርገው የሚታሰቡበት ኹነት ለተመጣጠነ ምግብ እጥረትና በእናትም ሆነ በጽንስ ላይ የአጭርና የረጅም ጊዜ ተጽዕኖ የሚፈጥር መሆኑ ተገልጿል። ይሁንና በሌላኛው ጎን እነዚህ በነውርነት የተፈረጁ ወይም የተከለከሉ ምግቦች ለእናትም ሆነ ለልጅ ያበርክታሉ ተብለው ከሚታሰቡ ማኅበረሰባዊ እይታ አንጻር ተቃኝቶ ለነውሮች መፈጠር ማኅበረባህላዊ ምክንያቶች አልታዩም። በዚህ ጥናት እንደተገለጸው ከእርግዝና ጋር በተያያዘ በሀገራችን ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ማኅበረሰቦች የነውር እሳቤዎች ተጠንተዋል፤ ይሁንና ከዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ጋር የተያያዙ የነውር ወይም የክልከላ እሳቤዎች ግን ትኩረት አልተሰጣቸውም። በመሆኑም ይህ ጥናት ይህን ክፍተት የሞላ ነው።

ኹለተኛው ደግሞ በ Ramulondi, እና ሌሎቹ (2021) የተካሄደ ሲሆን በእርግዝና ወቅት፣ በድህረ ወሊድና ሕፃናትን በመመገብ ዙሪያ ያሉ የምግብ ነውሮችን ተመልክቷል። በግኝቱ 64% ያህል የጥናቱ ተሳታፊዎች ይህን ባህላዊ ነውር ወይም ክልከላ የሚቀበሉ ሲሆኑ ከአንዳንድ ምግቦች ጋር የተያያዙ የምግብ ነውሮች በሳይንሳዊ ጥናት ያልተደገፉ ቢሆኑም አንዳንድ የምግብ ነውሮች ደግሞ ነፍሰጡር ሴቶችን ጤናማ ካልሆነ አመጋገብ የሚጠብቁ እንደሆኑ ተገልጿል። ከዚህ አንጻርም የዙሉ ሴቶች የአመጋገብ ሥርዓት ስኬታማና የሚመከር ነው የሚል መደምደሚያ አቀርቧል። ጥናቱ የምግብ ነውሮች ያላቸውን አዎንታዊና አሉታዊ ሚና ከሳይንሳዊ እይታ አንጻር መመልከቱ ከቀደመው የተሻለ ቢያደርገውም ከሳይንሳዊ ዕይታ ውጪ ነውሮች ለፈጠራቸው ወይም ለደነገጋቸው ማኅበረሰብ ይሰጣሉ ተብሎ የሚታሰበው ማኅበረ ባህላዊ ፋይዳ አልታየም። ከእርግዝና ውጪ በሌሎች ማኅበረ ባህላዊ አውዶች ያሉ የነውር እሳቤዎች አልተጠኑም።

ሌላው በነውር ላይ የተሠራው ጥናት ደግሞ በEmmanuel, (2013) ነውር ማኅበራዊ ሥርዓትን ለማስጠበቅ በነበረው ሚና ላይ በማተኮር ተሠርቷል። በዚህም በቃላዊ ልማዶችና በተጻፉት ላይ የተገለጹት ላይ ያተኮረ ሲሆን ነውር ዘላቂነት ያለው ማኅበራዊ ሥርዓትን እና ሥነምግባርን ለማግኘት የሚያስችል አስፈላጊ መሣሪያ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል። ይሁንና በሌሎች ቁሳዊ ባህሎች የተገለጸውን የነውር እሳቤ አልተመለከተም። ይህም ከተጠኚ ማኅበረሰብ ልዩነት ባለፈ በ Emmanuel, (2013) ጥናት ውስጥ የታየ ክፍተት ነው። በመሆኑም በዚህ ጥናት በዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ ያለውን የነውር እሳቤ በመመልከት የተጠቀሰውን ክፍተት ለመሙላት ተሞክሯል።

በሌላ በኩል የSharma, እና ሌሎቹ (2020) ጥናት ነውር የተፈጥሮ ሃብቶችን ለማስጠበቅ ባለው ሚና ላይ አተኩሮ ነውሮችን በመመደብ ሰንዷል። በግኝቱም በማኅበረሰቡ የተከለከሉ ድርጊቶችን ማክበር ከፍተኛ አጽንኦት የሚሰጠው ሲሆን እነሱን መስበር ደግሞ የእግዚአብሔርን ቁጣ ያመጣል ተብሎ ስለሚታመን ነውሮች የተፈጥሮ ሃብትን ለመጠበቅ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ጥናቱ አመላክቷል። ይሁንና በዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዙሪያ ያሉ ነውሮችንና ማኅበረባህላዊ ፋይዳቸውን አልተመለከተም።

Omobola; (2013) በደቡብ ምዕራብ ናይጄሪያ የዮሩባ ማኅበረሰብ ውስጥ ያለን የነውርና የአምልኮን አጠቃላይ ገጽታ ተመልክቷል። ነገር ግን በቁሳዊ ባህሎች ላይ ያለው የነውር እሳቤ ትኩረት አልተሰጠውም። እንዲሁም ሞላ ጀንበሬ (2009) የነውር እሳቤ በሊቦ ከምከም ወረዳ ማኅበረሰብ እምነት በሚል ርዕስ ባካሄዱት የፒ.ኤች.ዲ ማሟያ ጥናት የምግብ፣ የግብርና እና የሞት ነውሮችን በጥምረት ተመልክተዋል። ይሁንና የተጠቀሱት ጥናቶች በተገለጹት ጭብጦች ላይ ከማተኮራቸው ባለፈ አንዳቸውም በሀገረሰባዊ ዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ ስለሚታዩ የማኅበረሰቡ የነውር እሳቤዎች ላይ ጉዳያቸውን አላደረጉም፤ ከርእስ ጉዳይ መመልከቻ ዐውድ ከመለያየቱም ባለፈ በውጪ ሀገር የተካሄዱ ጥናቶች ነውሮችን የተመለከቱት ከእኛ ሀገር ማኅበረሰብ ባህል ውጪ ነው። ነውሮች ደግሞ የመደንገጋቸውም ሆነ የመጠበቃቸው ምክንያት ማኅበረ ባህላዊ ልማዶች በመሆናቸው ገጽታቸው ከሀገር ሀገር የተለያየ መሆኑ በተለያዩ ማኅበረሰቦች ተተኳሪነት እንዲጠኑ ያደርጋቸዋል። በመሆኑም በሰሜን አቸፈር ማኅበረሰብ የዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ ያለው የነውሮች እሳቤ መጠናቱ የነውሮችን ሌላኛ ማኅበረ ባህላዊ ገጽታ በማመላከት ክፍተትን ይሸፍናል። በሀገር ውስጥ ከተሠሩት ጥናቶች መካከልም የዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም የነውር እሳቤዎች ላይ ማተኮሩ እንዲሁም ከዝግጅትና አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ሌሎች ተዛማጅ ቃላዊና ልማዳዊ ድርጊቶችን መመልከቱና በፎክሎር የጥናት ዐውድ መቃኘቱ የተለየ ያደርገዋል። በመሆኑም ይህ ጥናት ይዞት በተነሳው ርዕሰጉዳይ ላይ ማተኮሩ ትኩረት ባልተሰጣቸው የነውር ገጽታዎች ላይ መረጃ ይሰጣል ተብሎ ታስቧል።

ለዚህ ጥናት በተደረገ የመስክ ቆይታ ወቅት የዕደጥበባቱ ዝግጅትና አጠቃቀም ልማድ የማኅበረሰቡ የነውር እሳቤዎች የሚታዩባቸው እንደሆኑ ታይቷል። ይህ ደግሞ ዕደጥበባቱ ከሚሰጡት ዘወትራዊ አገልግሎት ባለፈ በማኅበረሰቡና በቁሶች መካከል ስላለው ትስስር እንዲሁም ማኅበረሰቡ የአንዳንድ ዕደጥበባትን ዝግጅትና አጠቃቀም አስመልክቶ "ነውር ነው" በሚል እሳቤ የአዘጋጆችና የተጠቃሚዎች፣ የጊዜና የሁኔታ ክልከላዎችን የሚጥልበትን ምክንያት በማወቅ የሕይወት ፍልስፍናቸውን ለመረዳት ያስችላል። በመሆኑም ጥናቱ በተጠኘው ማኅበረሰብ የዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዓውድ ውስጥ የማኅበረሰቡን የነውር እሳቤ መተንተን የሚል አጠቃላይ ዓላማ ይዞ ተነስቷል። በተጨማሪም የነውሮችን ዓይነትና ይዘት መለየት፣ የነውሮችን ፋይዳ መመርመር፤ የነውር ጥሰትና ማኅበረባህላዊ አጸፋዎችን ማመላከት የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎችን ለማሳካት i) ማኅበረሰቡ ነውሮችን የፈጠረበት ምክንያት ምንድን ነው? ii) በዕደጥበባቱ ዝግጅትና አጠቃቀም ዙሪያ የተፈጠሩት ነውሮች ትኩረት ምን ይመስላል? iii) ለነውሮች ጥሰት የማኅበረሰቡ አጸፋ ምንድን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎችን መልሷል።

## 2. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ሥር የጥናቱ ጽንሰሃሳባዊና ንድፈሃሳባዊ መሠረቶች የቀረቡ ሲሆን የነውር ምንነት፣ ምድቦችና ማኅበረሰባዊ ፋይዳዎች በሚሉ ጽንሰሃሳቦች ዙሪያ አጠቃላይ ገለጻና ማብራሪያ ቀርቧል። በተጨማሪም ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች ሲተነተኑ መሠረት የተደረጉ ንድፈሃሳቦች ተገልጸዋል።

**2.1 የነውር ምንነት**

በዚህ ጥናት ውስጥ ነውር የሚለው ቃል የእንግሊዝኛውን Taboo ወይም ማኅበረባህላዊ ክልከላ የሚለውን እንዲወክል ተደርጎ አገልግሎት ላይ ውሏል። ምክንያቱም በተጠኚው ማኅበረሰብ ውስጥ ባህላዊ ክልከላ የተደረገባቸውን ነገሮች መተላለፍ "ነውር" ተብሎ የሚገለጽበት ሁኔት ስላለ ነው። "Taboo" ማኅበረ ባህላዊ ክልከላ /Sociocultural prohibition የሚል ፍች እንዳለው (Tylor 1871, 414-421) ገልጸዋል። በተመሳሳይ Taboo የሚለው forbeden/ክልከላ የሚል ጽንሰሐሳብ እንደያዘ (Freud 1919. 13-14) ገልጸዋል። ይህ ማኅበረባህላዊ ክልከላ በሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ "ነውር" ተብሎ ይገለጻል። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያሳተመው አማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፤ 344) ነውር የሚለውን "በኅብረተሰቡ ባህልና እምነት መሠረት እንደ መጥፎ ነገር የሚታይ የሚቆጠር ድርጊት፣ ምግባር፣ ገመና፣ ነውር ነው፣ ፀያፍ፣ መጥፎ ነው፣ ተገቢ አይደለም፣ ጥፋት ነው..." በማለት የሚበይነው ሲሆን ደስታ ተክለወልድ (1962፤ 1047) ነውር በሰው፣ በእንስሳት ገላ ላይ ያለ እብጠት፣ ጉድለት፣ ላይን የሚያስቀይም፣ ክፉ ግብር፣ ኃጢአት፣ ስካርን፣ ምንዝርን የመሰለ በማለት ብያኔ የሰጡት ሲሆን ነውር ነው ሲባልም እንኳን ሊሠሩት ሊሰሙት አይገባም የሚል ፍች በመስጠት ነውር የሚለው የተከለከለ የሚል ፍች እንዳለው አመላክተዋል። ይህም የእንግሊዘኛውን Taboo በቀጥታ ትርጉሙ ክልከላ የሚለውን የሚተካበትን ሁኔት የሚጠቁም ነው። ኪዳነወልድ ክፍሌ (1948፤ 633) ነውር የሚለውን በግብር ወይም በነገር ጸያፍ መሆን ወይም መባል የሚል ፍቺ ከሰጡት በኋላ ነውር በቁሙ የመልክ፣ የግብር፣ የሕዋስ ሕጸጽ፣ ገመና የሚል ፍቺ እንዳለውም አክለው ገልጸዋል። ከቀረቡት ብያኔዎች ነውር የሚለው እሳቤ በአካላዊ፣ ስሜታዊና ድርጊታዊ ሁነቶች የሚንጸባረቅ እንደሆነ መረዳት ተችሏል። በዚህ ጥናት ውስጥም በዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም አውድ ውስጥ ያሉ ድርጊት ተኮር ነውሮች ወይም ክልከላዎች ተተኳሪ ተደርገዋል።

ኪዳነወልድ (1948፤ 962) "ሕሩም" የሚለውን ቃል የተከለከለ የሚል ፍች ሰጥተውታል። ጥናቱ የእንግሊዝኛውን Taboo/ክልከላ እንዲሁም አማርኛውን "እርም" የሚሉትን በቀጥታ ያልተጠቀመበት ምክንያት ማኅበረሰቡ ዕደጥበባቱን ሲያዘጋጅና ሲጠቀም የሚደነግጋቸውን ክልከላዎች "ክልክል ነው" ወይም "እርም ነው" ብሎ ሳይሆን ሚገልጻቸው "ነውር ነው፣ ያስነውራል፣ ትነወራለች፣ ይነወራል... ስለዚህ አይደረግም" እያለ ነው። የባህል ጥናት ደግሞ የሚጠናው ጉዳይ በተጠኚው ማኅበረሰብብ ቋንቋ እንዴት ይገለጻል? እና ምን ዐይነት ስያሜ አለው? የሚለውን መመልከት እንዳለበትና ከማኅበረሰቡ ልማዳዊ አጠቃቀምና እሳቤ አንጻር መቃኘት እንዳለበት ይመከራል (ፈቃደ 1991)። በመሆኑም ይኽን የባህል ጥናት አውዳዊ አጠቃቀም መሠረት በማድረግ የእንግሊዝኛው Taboo ወይም ማኅበረባህላዊ ክልከላ በሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ "ነውር" ተብሎ የሚገለጽበት እሳቤ ስላለ የማኅበረሰቡን አጠቃቀም በማስቀደም እነዚህን ቃላት ጎን ለጎን መጠቀም ግድ ብሏል። በመሆኑም በእንግሊዝኛ ቋንቋ Taboo በሚል የተጻፉ ጽንሰሃሳቦች ማኅበረሰቡ ነውር እያለ የሚገልጻቸውን የዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ክልላዎቸች እንዲያብራሩ ተደርገው አገልግሎት ላይ ውለዋል።

Sharma እና ሌሎቹ (2020:575) ደግሞ ነውር በልማዳዊ እምነቶች ላይ የተመሠረተ እንደሆነ በመግለጽ በእንግሊዝኛው Taboo 'tapu' ከሚለው የፖሎኒዥያ ቃል የተወሰደ ሲሆን በአጠቃቀም ላይ የተጣለ እገዳ እንደሆነ ይገልጻሉ። በተመሳሳይ Fershtman እና ሌሎቹ (2009፡2-5) Taboo/ነውር የሚለው የፖሎኒዥያ ስርመሠረት ያለው ቃል እንደሆነ ከገለጹ በኋላ እምነትን መሠረት ያደረገ የድርጊት ክልከላ በማለት ገልጸውታል። ይህ የድርጊት ክልከላ የሚለው ከላይ በተጠቀሱት የአማርኛ መዝገበ ቃላት ላይም የተሰጠ ብያኔ ነው። ከቀረቡት ገለጻዎች እንደምንረዳው ነውር ማኅበረሰቡ ከራሱ ልማዳዊ እምነት በመነሳት ማኅበራዊ ደኅንነቱን ለማረጋገጥ ሲልና ለደህንነቱ አስጊ መስሎ የተሰማውን ድርጊት እንዳይፈጸም የሚከለክልበት ገደብ መሆኑን ነው። ይኸውም Sharma እና ሌሎቹ 2020:575) እንደገለጹት የነውር መነሻው/መሠረቱ ማኅበረሰባዊ እምነት ሲሆን ማኅበረሰቡ ይህን ባደርግ እንዲህ ያለ ጥፋት/ቅጣት ይደርስብኛል ብሎ በማመን ከእኒህ ጥፋቶች/መጥፎ ነገሮች ለመጠበቅ ሲል ነውሮችን እንደሚደነግግ የሚያመለክት ነው። አያይዘውም ማኅበረሰቦች ለኗሪዎች ተቀባይነት ያላቸው እሴቶችን በማውጣትና እንዲከተሏቸው በማበረታታት፤ የሰዎች ባህርይም ሆነ አመለካከት በእነዚህ ደንቦች እንዲቀረጽና እንዲመራ እንደሚያደርጉ፤ እነዚህ የባህርይ መመሪያዎችም በተለምዶ እንደ ማኅበራዊ ደንቦችና ነውሮች ወይም ክልከላዎች የሚጠቀሱ መሆናቸውን ገልጸዋል። በተጨማሪም የአፈንጋጭነትን ጸባይ ለመከላከል ብቸኛው መንገድ ግለሰቦች ያንን ድርጊት እንዳያስቡ ጭምር የሚያደርግ መሆኑን በመግለጽ የነውሮችን መፈጠር ምክንያት ያብራራሉ። በዚህ ጥናትም በሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ የህገረሰባዊ ዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዓውድ ውስጥ የተደነገጉ ክልከላዎች ምንነትና መነሾዎቻቸው ይተነተናሉ።

### 2.2 የነውር ምደባ

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ማብራሪያ ማቅረብ የተፈለገበት ምክንያት የነውር ምደባ አብዛኛውን ጊዜ አንድ ማኅበረሰብ ነውሮችን የፈጠረባቸውን ዐውዶችና ምክንያቶች መሠረት ስለሚያደርግ ነው። ይኸውም ተጠኚው ማኅበረሰብ የፈጠራቸው ነውሮች ወይም ማኅበረባህላዊ ክልከላዎች በየትኛው የዕደጥበብ ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ምን ዓይነት ማኅበረ ባህላዊ አመክንዮ ያላቸው ናቸው? የሚለውን ለመመልከት የረዳ ጽንሰሃሳብ በመሆኑ ነው። የነውር እወጃ ወይም ማኅበረባህላዊ ክልከላ አጠቃቀም ኹለት መልክ ሊኖረው እንደሚችል (Osei, 2006: 43) ይገልጻሉ። ይኸውም አንደኛው ከአምልኮ ሥርዓት ወይም ከንጹሕነት ጋር ያተያያዘው የአጠቃቀም ዐውድ ሲሆን ሌላው ደግሞ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ የአጠቃቀም ዐውዶችን እንደሚወክል ይገልጻሉ። በመሆኑም የነውሮች ወይም ክልከላዎች ምደባ ሲነሳ ነውሮችን የፈጠራቸው ወይም የደነገጋቸው ማኅበረሰብ የሚጠቀምበትን ዐውድና ድንጋጌዎችን የሚያስጠብቅበትን ምክንያቶች መሠረት እንደሚያደርግ የሚጠቁም ነው። ይህ ደግሞ ወጥ የሆነ የነውሮች ምደባ እንዳይኖርና ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ የተለያየ አጠቃቀማዊ ምድብ እንዲኖራቸው ያደርጋል። ይህ ከመሆኑ የተነሳም በነውር ላይ ጥናት ያካሄዱ ተመራማሪዎች ነውሮችን ከተደነገጉበት ማኅበራዊ ሁነት/ዘርፍና ማኅበረሰቡ ነውሮችን ወይም ክልከላዎችን በመደንገጉ እጠበቃለሁ ብሎ ከሚያምነው ነገር ወይም ከሚኖራቸው ፋይዳ አንጻር ሲከፋፍሏቸው ይታያሉ። ለአብነትም ሞላ (2009) ነውሮችን ከተፈጠሩበት ማኅበራዊ ሁነት/ዘርፍ አንጻር የምግብ፣ የሞትና የግብርና ነውሮች ብለው ከፍለዋቸዋል። በሌላ

በኩል Omobola (2013) ነውሮችን ከታወጁበት ማጠንጠኛ ጭብጥ አንጻር ከአደጋ ጋር የተያያዙ፣ ታላላቆችን ከማክበር ጋር የተያያዙ፣ ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ፣ ከንጽሕና ጋር የተያያዙ፣ ከሞራል እሴቶች ጋር የተያያዙ፣ አባካኝነትን የሚቃረኑና ለመግለጽ አስቸጋሪ ከሆኑ ጋር በማለት ከፋፍለዋቸዋል። Emmanuel (2013) በደቡብ ምዕራብ ናይጀሪያ በቀደሙት የኦንዶ ማኅበረሰብ ውስጥ ነውሮች ማኅበራዊ ሥርዓትን ለማስከበር ባላቸው ሚና ላይ ባደረጉት ጥናት ውስጥ ካላቸው ጠቀሜታ አንጻር የመንግስትን/የአስተዳደር ደህንነትን የሚያረጋግጡ፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓትን የሚያስተምሩ፣ የልጆችን ሥነምግባር የሚያንጹ፣ ንጽሕናን የሚያስጠብቁና የወንጀል ቁጥጥርን የሚያጠነክሩ በማለት ከፍለዋቸዋል። ከቀረቡት የነውሮች ምድብም ነውሮች የተፈጠሩበት ዘርፍ፣ ማጠንጠኛ ጭብጣቸው/ይዘት እንዲሁም ለማኅበረሰቡ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ እንደ መከፋፈያ መስፈርት ያገለገሉ መሆናቸውን ነው። በዚህ ጥናትም ተጠኚው ማኅበረሰብ ነውሮችን ከፈጠረበት ዐውድ በመነሳት የነውሮች አፈጣጠር ማኅበረባህላዊ አመክንዮዎች ትንተና ቀርቦባቸዋል።

### 2.3 የነውር እወጃ ማኅበረሰባዊ ፋይዳ

ከባህል ጥናት አቀራረቦች መካከል የባህሪያዊያን አቀራረብ (behaviourist approach) ማኅበረሰቡ ምን ይፈቅዳል? ምን ደግሞ ይከለክላል? የሚለውን የሚመለከት ሲሆን የጠቀሜታዊነት ወይም ተግባርያዊነት አቀራረብ (functionalist approach) ደግሞ ከፈቃዱና ከክልከላው ጀርባ ያሉ ምክንያቶችን የሚመለከት ነው (Katan 1999)። ይህ ደግሞ ማኅበረሰቡ ነውሮችን ወይም ክልከላዎችን የደነገገበትን ምክንያት የሚያመላክት ሲሆን ማኅበረሰቡ አንድን ፎክሎራዊ ክዋኔ የሚፈጥርበትና የሚያስቀጥልበት ምክንያት ማኅበረሰባዊ መዋቅሩን ለመጠበቅ አንዳች ፋይዳ ይጨምርልኛል ብሎ ሲያስብ ነው ከሚለው የመዋቅራዊ ጠቀሜታዊነት ንድፈሃሳብ ዕይታ ጋር የሚዛመድ ነው።

ነውሮች በተፈጠሩበት ዐውድ ውስጥ ማኅበራዊ፣ ሥነምግባራዊና ሳይንሳዊ ጠቀሜታ እንደሚኖራቸው (Osei, 2006) ገልጸዋል። Sharma et al. (2020: 575) በምዕራብ ሂማሊያ ነውሮች በአጠቃላይ ከቦታ፣ ከሰው፣ ከእምነት ወይም ከልማድ/ወግ ጋር የተቆራኙ እንደሆኑ ቁልፍ ለሆኑ ባህላዊ እሴቶች ትምእርት መሆናቸውንና በከፍተኛ ደረጃ ስር የሰደደ ማኅበራዊ ሥነምግባርን የሚቀርጹ እንደሆኑ ይገልጻሉ። Emmanuel (2013: 95-98) ነውር ዘላቂነት ያለው ማኅበራዊ ሥርዓትና ሥነምግባራዊነትን ለማግኘት የሚያስችል አስፈላጊ መሣሪያ ነው ካሉ በኋላ በቀደመው የኦንዱ ግዛትና በሌሎች የአፍሪካ ማኅበረሰቦች ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን ከሚጠቀሚቸው ዘዴዎች መካከል እንደሚጠቀስ ገልጸዋል። ይኸውም በማኅበረሰቡ እንዳይፈጸሙ የሚፈለጉ ኢ-ግብረገባዊ ድርጊቶችን ነውር አድርጎ በመፈረጅ ወይም በመከልከል ማኅበረሰባዊ መዋቅሩ የተረጋጋ እንዲሆን የሚያደርጉበት ዘዴ እንደሆነ ገልጸዋል። ይኸም ነውር ማኅበረሰባዊ ደህንነትን በማስጠበቅ በኩል ያለውን ሚና የሚያመለክት ነው። በአጠቃላይ ከቀረቡት ገለጻዎች ነውሮችን ወይም ክልከላዎችን የመደንገግ ጠቀሜታ ማኅበረሰቡ ነውሮችን ከደነገገባቸው ምክንያት አንጻር የሚታይና ማኅበረ ባህላዊ መሠረት ያለው መሆኑን መረዳት ተችሏል። በዚህ ጥናትም የሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ በዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ ነውሮችን ወይም ክልከላዎችን የደነገገበትን ምክንያቶች መነሻ በማድረግ ማኅበረሰቡ ከዚህ ድንጋጌ አገኛለሁ ብሎ የሚያስባቸውን

ፋይዳዎች ለማመላከት ተሞክሯል። ዐውድ ሲባልም ነውሮቹ ወይም ክልላዎች የደነገጉበትን ማኅበረሰብ ባህል፣ልማዳዊ እምነት የነውሮች እወጃ ወይም ማኅበረባህላዊ ክልከላዎች የተፈጠሩበትን ሁነት/ዘርፍ እንዲሁም ምክንያት መሠረት የሚያደርግ ነው።

#### 2.4. ንድፈሃሳባዊ መሠረቶች

ከተጠኚ ማኅበረሰቦች የተሰበሰቡት መረጃዎች በማኅበራዊ ግንባታና በመዋቅራዊ ጠቀሜታዊነት በጥምረትም በግላጼያዊና ህቡዑ ተግባራዊነት ንድፈሃሳቦች ተቃኝተው ተተንትነዋል። በዚህ የጥናት ዐውድ ውስጥ ማኅበረሰቡ በዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ ምን ዓይነት ነውሮችን ወይም ክልከላዎችን ፈጠረ? ለነውሮች መከሰት ምክንያት ምንድን ነው? የተከለከሉ ነገሮችን መተላለፍ የሚያስከትለው ማኅበረባህላዊ አጸፋ ምንድን ነው? የሚሉት ተተንትነዋል። የማኅበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ ማኅበረሰባዊ ዕውቀትና እምነቶች የተፈጠሩበትን መንገድ፣ መሠረትና አመክንዮን የሚመለከት ነው። ይኸውም እንደ Berger እና Luckman (1966) ገለጻ የማኅበራዊ ግንባታ ንደፈ ሃሳብ ዕውቀትና ፍቺ ማኅበራዊ ሥሪቶች ናቸው የሚል ሲሆን የኅብረተሰብ እውቀት ጥናት ይህ ሁኔታ በምን ሂደት ውስጥ እንደተፈጠረ ወይም መሠረቱ ምን እንደሆነ ማጥናት/መተንተን አለበት የሚል ነው። ስለሆነም በዕደጥበባቱ ዝግጅትና አጠቃቀም ዙሪያ የተፈጠሩ ነውሮችን ለመመልከት እንዲሁም ይህ ማኅበረሰባዊ ግንዘቤ/ዕውቀት የሚገነባው በማኅበረሰቡ መረዳት ልክ ስለሆነ የሚዳኘውም በማኅበረሰቡ ነው ስለሚል በነውሮች ጥሰት ዙሪያ ያለውን ማኅበረሰባዊ አፀፋ ወይም ቅጣት ለመመልከት ይህ ንድፈሃሳብ አገልግሎት ላይ ውሏል። በተጨማሪም ነውሮች የማኅበረሰቡን መዋቅራዊ እሴት ለማስጠበቅ ያላቸውን ፋይዳ ለመመልከት የRadcliffe Brown (1952) የመዋቅራዊ ጠቀሜታዊነት ንድፈሃሳብ አገልግሎት ላይ ውሏል። የመዋቅራዊ ጠቀሜታዊነት ንድፈ ሃሳብ አንድ ፎክሎራዊ ቅርጽ በሚከወንበት ፎክ ቡድን ወይም ማኅበረሰብ አደረጃጀት ውስጥ ያለውን ፋይዳ የሚመለከት ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ነውሮች የተፈጠሩበትን ተቀዳሚ ተግባርና ህቡዑ ተግባር ለመመልከት የMerton[4] (1968, 73-114) የግላዜያዊ/ተቀዳሚ ተግባር (manifest function) እና የኅቡኣዊ ተግባር (latent function) እሳቤዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል።

## 3. የጥናቱ ሥነዘዴ

ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ተከትሏል። ይህ ዘዴ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ መቼ? የት? ለምን? እንዴት? በማን? ተከወነ ወይም ይከወናል? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጡ ዓይነታዊ መረጃዎች የሚቀርቡበት የምርምር ዘዴ ነው። በመሆኑም በተጠኚው ማኅበረሰብ የዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ የነውር እሳቤ ምን ዓይነት ገጽታ አለው? ከየትኛው የዕደጥበብ ዝግጅት ወይም አጠቃቀም ጋር የተያያዘ ነው? ለነውሮች መፈጠር መነሻ የሆነው ማኅበረባህላዊ አመክንዮ ምንድን ነው? የሚሉትን ጉዳዮች የሚያብራሩ፣ የሚገልጹና የሚተነትኑ መረጃዎች ቀርበዋል። ከዚህም አንጻር በሰሜን አቸፈር ወረዳ ከሚገኙ የይስማላ፣ ይስማላ ጃንኪት፣ ኳላ ባካ፣

[4] manifest function and latent function የሚሉት ግላዜያዊ ተግባርና ኅቡኣዊ ተግባር የሚል የትርጉም አቻ የተሰጣቸው ሲሆን በትንተናው ክፍልም በዚህ ስያሜ አገልግሎት ላይ ውለዋል።

ይብሊተረፊት፣ ጭንባ፣ ቢዝራ ጡዳ፣ ወንበርያ ባርካንታ፣ ሳንክራ ቀበሌዎች በዓላማ ተኮር ንሞና 16 መረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል።

ከላይ በባህሪያዊያን አቀራረብ እንደተገለጸው ክልከላዎች ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ የሚለያዩበትና አንዱ የሚፈቅዳቸውን ሌላው የሚከለክልበት ሁነት እንደሚኖር ተገልጿል። በተጠቀሱት ቀበሌዎችም ከዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ነውር ተብለው የተደነገጉ ክልከላዎች እንዳሉ መመልከት ተችሏል። ይሁንና በሁሉም ቀበሌዎች ተመሳሳይ የሆነ የነውር እወጃ ወይም ክልከላ አለ? ወይስ የተለያየ? የሚለውን በስብጥር ለማየት በናሙናነት ተመርጠዋል። ይህ የተደረገበት ምክንያትም በአንዳንድ ቀበሌዎች ያሉ የዕደጥበባት አዘጋጆች ሙያውን የለመዱበት መንገድ የተለያየ መሆኑ ማለትም በዘር ሃረግ መሠረት በተዋረድ የተቀበሉና ለገቢ ምንጭ ሲሉ የለመዱ በመኖራቸው በእነዚህ ሙያተኞች መካከል ያለው የነውር/ማኅበረባህላዊ ክልከላ እሳቤ ምን ይመስላል? የሚለውን በስብጥር ለመመልከት ነው። የእነዚህ መረጃ አቀባዮች ምርጫ ፆታንና ሙያን ያሰባጠረ ሲሆን በማኅበረሰቡ ውስጥ የሸክላ ቁሶችን በማዘጋጀት የሚታወቁ ቡድኖች እንዲሁም እንደ ስፌትና ፈትል ሌሎችንም የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን የሚያዘጋጁና የሚጠቀሙ የማኅበረሰቡ አባላት የጥናቱ ተሳታፊዎች ተደርገዋል።

ምልከታ ቃለመጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይት መረጃዎችን ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ ውለዋል። ይኸውም ዕደጥበባቱ በሚዘጋጁበት ቦታ በመገኘት በዐውዱ ውስጥ እንዳይፈጸሙ የሚከለከሉ ድርጊቶችን በመመልከት ለምሳሌ በሸክላ ቁሶች ዝግጅት ወቅት የሚከለከሉ ድርጊቶችን ማለትም ሥራውን ከጫጫታና ከሰው ዐይን ለማራቅ የሚያደርጉትን ጥረት በተዐቅቧዊ ምልከታ መረጃ መሰብሰብ ተችሏል። በስፌት ቁሶች ዝግጅት ዐውድ ውስጥ ደግሞ በተሳትፏዊ ምልከታ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በሸክላ ቁሶች ዝግጅት ዐውድ ውስጥ ተአቅቧዊ ምልከታ የተካሄደበት ምክንያት ከሸክላ ገድና የክፉ ዐይን ተጋልጦ ጋር በተያያዘ ከባለሙያዎች ውጪ ማንኛውንም ሰው የማያሳትፍ ልማዳዊ እምነት ወይም ክልከላ በመኖሩ ነው። በዕደጥበባቱ ዝግጅትና አጠቃቀም ዙሪያ የተፈጠሩት የማኅበረሰቡ ነውሮች ወይም ክልከላዎች መሠረታቸው ምንድን ነው? ለማኅበረሰቡ የሚሰጡት ፋይዳስ ምንድን ነው? እንዲሁም ነውሮች ወይም ክልከላዎች ቢጣሱ ከማኅበረሰቡ የሚሰነዘረው አጸፋ/ቅጣት ምን ሊሆን ይችላል? ለሚሉት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ደግሞ በነጻ ቃለ መጠይቅ መሰብሰብ ተችሏል። እንዲሁም የሸክላ ቁሶችን ዝግጅትና አጠቃቀም አስመልክቶ በይስማላ ቀበሌና በወንበርያ ባርካንታ ቀበሌዎች በሚገኙ ባለሙያዎች ዘንድ ለታየው የነውር እሳቤ ልዩነት መሠረቱ ምንድን ነው? የሚለውን ለማጥራት በ09/02/2015ዓም በወንበርያ ባርካንታ ቀበሌና በ25/02/2015ዓ.ም በይስማላ ቀበሌ የሸክላ ባለሙያዎችን ተሳታፊ ያደረገ የቡድን ተኮር ውይይት ተካሂዷል።

የሰሜን አቸፈር ወረዳ በአማራ ክልል ሰሜን ጎጃም ዞን ከሚገኙ 7 ወረዳዎችና ሦስት ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ አንዱ ወረዳ ሲሆን ዋና ከተማውም ሊበን በመባል ይታወቃል። ሊበን ከክልሉ ርዕሰ ከተማ ባህርዳር በ104 ኪ.ሜ ከአዲስአበባ ከተማ ደግሞ በ 532 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል። ወረዳው በደቡብ ደቡብ አቸፈር ወረዳ፣ በሰሜን ጣና ሀይቅ፣ በምስራቅ ሜጫና ባህርዳር ዙሪያ

ወረዳ እንዲሁም በምዕራብ የሰሜን ጎንደር ዞን አለፋ ወረዳ ያዋሱኑታል (ከሰሜን አቸፈር ወረዳ ፕላን ኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት ከወረዳው ካርታና መግለጫ የተገኘ፣20/01/2014 ዓ.ም)።

## 4. በዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ የታዩ የነውር እሳቤዎች ትንተና እና ውይይት

ይህ ክፍል በሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ የሀገረሰባዊ ዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ የታዩ የነውር ዓይነቶች፣ ነውሮች ወይም ከልከላዎች የታወጁበት/የተደነገጉበት ምክንያትና ሚናቸው፤ ነውሮችን ተላልፎ በተገኘ ሰው ላይ የሚሰነዘሩ ማኅበረሰባዊ ቅጣቶችን አስመልክተው የተሰበሰቡት መረጃዎች የተተነተኑበት ሲሆን እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 4.1. የዕደጥበባት አዘገጃጀትን መሠረት ያደረጉ የነውር ዓይነቶች

በሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ የዕደጥበባት ዝግጅት ዐውድ ውስጥ የታዩ የነውር ዓይነቶች በሸክላና በስፌት ቁሶች የዝግጅት ዐውድ ውስጥ የታዩ ናቸው። በመሆኑም እንደሚከተለው በቅደምተከተል ቀርበዋል።

#### 4.1.1 በሸክላ ቁሶች የዝግጅት ዐውድ ውስጥ የታዩ የነውር እሳቤዎች

በዚህ ዐውድ በቀዳሚነት የሚጠቀሰው የነውር ወይም የክልከላ ይዘት በረከትን ወይም ገድን ያርቃሉ ተብለው የሚታሰቡ ናቸው። በሰሜን አቸፈር ማኅበረሰብ የሸክላ ባለሙያዎች ዘንድ ባለሙያዋ ያለማቋደሻ/ጉዝጉዞ[5] እና ያለ ጌጣጌጥ ቁሶችን እንድታዘጋጅ አይፈቀድላትም። ይኸን መተላለፍ ገድን ያርቃል ተብሎ ይታመናል። እንደማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት እነዚህን ድርጊቶች አለመፈጸም የሸክላ ቁሶች ተሠርተው በሚደርቁበትና በእሳት በሚተኮሱበት ወቅት የመፍረስ አደጋ ይገጥማቸዋል፤ ገበያ በሚወጡበት ጊዜም የመሸጥ ገድን ያርቃሉ ተብሎ ይታሰባል። በመሆኑም ገና የሸክላ አፈር በሚቆፈርበት ጊዜ የቂጣ ቆረሳ በመፈጸም፤ ጭቃው ተቦክቶ ቁሶቹ በሚሰሩበት ጊዜና ወደ ገበያ በሚወጡበት ጊዜ ደግሞ ቡና ተፈልቶ፣ ጠላና አረቄ ቀርቦ፣ ሰንደል ተጭሶ ጉዝጉዞ ይደረጋል። ይህ ድርጊትም በሸክላ አፈር ላይ ያለውን የገድ መንፈስ ደስ ስለሚያሠኘው ሥራው የሰመረ እንዲሆን ያደርጋል ተብሎ ይታመናል። በአንጻሩ ይህ መማለጃ ካልቀረበ ደግሞ በዝግጅት ወቅት ሸክላው እንዲሰበር፤ በሽያጭ ወቅትም እንዳይሸጥ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል።

> ገና ከመሥራትሽ በፊት ቡናሽን ታፈያለሽ፣ ሰንደልሽን ታጨሻለሽ፣ አረቂ ካለ ታቀርቢያለሽ ጠላም ካለ ይቀርባል፤ ማልዳ ማለት ነው ስትገቢ ወደ ሥራ ስታበቂም እንደዛ ይፈልጋል፤ ተተጣጥበሽ ቡናሽን ታፈያለሽ ዝም ብሎ በደረቅ አይወድም። ንዝንዝ ነገር አይፈልግም ስቀሽ ስትሠሪው ነው ሚወጣው፤ ስቀሽ ደስ ብሎሽ ገበያ ስትወጪ ይቀናሻል እያማረርሽ ብትወጪ መልሰሽ ነው

[5] በሚሠራው የሸክላ አፈር ላይ ያለው የገድ/የመልካም አጋጣሚ መንፈስ ደስ እንዲለውና ሸክላው ሳይሰበር እንዲወጣና ቶሎ እንዲሸጥ በሚል እሳቤ ሥራ ከመጀመሩና ከተፈጸመ በኋላ የሚቀርብ ምግብና መጠጥ

> ምታመጪው፤ እንደ ቲሽት/ውቃቢ ነገር አለው፤ (ወ/ሮ ጌጤ፣ ቃ.መ.፣ 03/01/2015ዓ.ም፣ ይስማላ ቀበሌ)።

ይህ ከልማዳዊ እምነትና ከነውር እሳቤ ጋር የተያያዘው የሸክላ ቁሶችን ደህንነት የመጠበቅ እሳቤ ማኅበራዊ መሠረት ያለው እንደሆነ መረዳት ተችሏል። ማኅበረሰቡ ይህን ማኅበረባህለዊ ክልከላ ወይም የነውር እሳቤ ሲፈጠር ከቁሶቹ ደህንነትና ከገበያ ገድ ጋር የተያያዘ ግላዊያዊ ወይም ተቀዳሚ ተግባር ስጥቶ ሲሆን ከዚህ ጀርባ እነዚህ ክልከላዎች ማኅበረሰባዊ ሰላምና መረጋጋትን በማስጠበቅ በኩል እንዲሁም የአካልና የመንፈስ ንጽህናን የመገንባት ኅቡኣዊ ተግባር እንዳላቸው መረጃዎች አመላክተዋል።

ሌላኛው ከሸክላ ቁሶች ዝግጅት ጋር በተያያዘ የታዩ የነውር ወይም የክልከላ ይዘቶች ከክፉ ዐይን ተጋላጭነት ጋር የተያያዙ ናቸው። በሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ ውስጥ በሚኖሩ ሸክላ ሠሪዎች ዘንድ ግርግር፣ የሰው ዐይንና ጫጫታ በሚበዛበት ቦታ የሸክላ ቁሶችን ማዘጋጀት የተከለከለና እንደነውር የሚቆጠር ተግባር ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት የሸክላ ሥራ ጫጫታ፣ ግርግርና የሰው ዐይን አይወድም ተብሎ ይታመናል። ይህም የሚባለው የሸክላ/የጭቃው ቲሽት[6] ግርግርና ዐይን ስለማይወድ በሚሠራበት ጊዜም ሆነ ሲተኮስ ይፈርሳል/ ይሰበራል ብለው ስለሚያምኑ ነው።

> ሸክላ ሲሠራ ብዙ ዐይን አያስፈልገውም፤ አሁን ቅድም አብረውሽ የመጡትን አሽከሮች[7] አስመልሻቸው ያልሁሽ ዐይን ስለማይወድ ነው። የሰው ዐይን ይሰብረዋል፤ አሁን እዛ አገሬ እያለሁ[8] ጓደኛ አንዳንዱ ሲያወጋን[9] ደጃፉን[10] ትተን እንደዛ በጓሮ ተገን ብየ/ተደብቄ ነው ምሠራ እና የሰው ዐይን ብዙም አይወድም፤ እንደ ሾተለይ ያደርገዋል (የአቶ ደጉ መንግስቴ ባለቤት[11]፣ ምልከታና ቃ.መ. 03/13/2014ዓ.ም፣ ይስማላ ቀበሌ)።

በማለት ሸክላና ሰው ሥሪቱ ከአፈር ነው። ሰው ከሰው ዐይን ውስጥ ከገባ እንደሚታመምና ከጸናበትም ለሞት ያደርሰዋል ተብሎ ይታመናል። ሸክላም የሰው ዐይን አይወድም ዐይን ከበዛበት ዓይነት[12] ይበላውና ይፈርሳል የሚል እምነት እንዳላቸውም ገልጸዋል። በተመሳሳይ ወ/ሮ ጌጤ የተባሉ ሸክላ ሠሪ ልክ እንደ ሰው ባህርይ ሁሉ ሸክላ ሥራም ጭቅጭቅና ጨኸት እንደማይወድ ሲሠራም ሆነ የተሠራው ገበያ በሚወጣበት ጊዜ ከጭቅጭቅ ርቀው በተቻላቸው መጠን ደስ የሚል

---

[6] የጭቃ መንፈስ ወይም ውቃቢ

[7] በማኅበረሰቡ ልማድ ልጅ እግር ወይም ጉብል የሚለውን ለመተካት የሚጠቀሙት ቃል ነው።

[8] ባለሙያዋ አሁን ካሉበት ተጠኚ ቀበሌ/ይስማላ መኖር ከመጀመራቸው በፊት ሻንብላ የተሰኘ የገጠር ቀበሌ ይኖሩ ነበር።

[9] ሲያወራን ወይም ሲያጫውተን የሚለውን ለመግለጽ የተጠቀሙት ቃል ነው።

[10] በፊት ለፊት በር እየሠራን ከነበረ ሰው ሲመጣብን በኋለኛው በር ተደብቀን እንሠራለን ሲሉ የተናገሩት ነው።

[11] መረጃ ሰጪዋ ስማቸው እንዳይጠቀስ ስለፈለጉ ፍላጎታቸውን በማክበር የመረጡትን ስያሜ መጠቀም ተችሏል።

[12] ዐይናቸው ላይ ክፉ መንፈስ ያላቸው ሰዎች ሰውንም ሆነ የሚያምር ቁስን ካዩ መንፈሱ ስለሚጋባ የታየው ነገር ለአደጋ ይጋለጣል ተብሎ ይታመናል። በዚህ ጊዜ ዐይነት በላው/የሰው ዐይን ገባበት ይባላል።

ድባብ ለመፍጠር እንደሚሞክሩና ረድኤት የሌለው/የስስት መንፈስ ያለበት ዐይን ሲያየውም እንደሚፈርስ በአንጻሩ የአንዳንድ ሰው ዐይን ደግሞ የገድ መንፈስ ያለው ወይም መልካም እድልን የሚያመጣ እንደሆነ ገልጸውልኛል። በተጨማሪም ማኅበረሰቡም ይህን አመለካከታቸውን ስለሚያውቅ በሚሠሩበት ጊዜ ድንገት ሰው ቢመጣ ከመግባታቸው በፊት ፈቃዳቸውን እንደሚጠይቋቸው ይናገራሉ፤(ምልከታና ቃ.መ. 03/01/2015ዓ.ም፣ ይስማላ ቀበሌ)። ከመረጃው መረዳት እንደተቻለው ሸክላ ልክ እንደሰው ለክፉ ዐይን ተጋላጭ ተደርጎ የታሰበበት መንገድ የሸክላ ቁስን ሥሪት ከሰውልጅ ባህርያተሥጋ ጋራ የሚያመሳስሉበት ምልከታ በመኖሩ ነው። በማኅበረሰቡ የሸክላ ቁሶች ዝግጅት ሂደት አፈር መቆፈር፣ ማቡካት ሠርቶ በነፋስና በፀሐይ ማድረቅ እንዲሁም መተኮስ ከሰውልጅ የመሬትነት፣ የውሃነት፣ የነፋስነትና የእሳትነት ባህርይ ጋር የተቆራኘ ተምሳሌት አለው። ይህ የአፈርነት/የመሬትነት ባህርይም ለክፉ ዐይን ተጋልጦና የመፍረስ አደጋ ይዳርጋል ተብሎ እንደሚታመን መረዳት ተችሏል።

ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው ማኅበረሰቡ በሸክላ ቁሶች ዝግጅት ዐውድ ውስጥ ጫጫታና የሰው ዐይን እንዳይኖር የሚከለክልበት ምክንያት በአፈሩ ላይ ያለውን ቲሽት ወይም ጠባቂ መንፈስ ስለሚረብሽ ቁሶችን እንዲሰበሩ ያደርጋል የሚል ስጋት ስላላቸው ነው። በመሆኑም የክልከላው ግላዊያዊ ወይም ተቀዳሚ ተግባር (manifest function) የቁሶችን ደህንነት ማስጠበቅ ሲሆን ኅቡኣዊ ተግባር (latent function) ደግሞ ባለሙያዎች በሥራ ወቅት ከሰው ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት የተገደበ ከሆነ ሥራቸው ላይ እንዲያተኩሩ ስለሚያስችላቸው የተቀላጠፈ ተግባር እንዲፈጽሙ ያስችላቸዋል የሚል እሳቤን የያዘ ነው። ጫጫታና ጸብን የማራቅ እሳቤውም የሸክላ ቁሶችን ደህንነት ከማስጠበቅ ባለፈ ቤተሰባዊ ብሎም ማኅበራዊ ደህንነትን ከማረጋገጥ አንጻር ኅቡኣዊ ተግባር ያለው መሆኑን መረዳት ተችሏል።

#### 4.1.2 በስፌት ቁሶች የዝግጅት አውድ ውስጥ የታዩ የነውር/ማኅበረባህላዊ ክልከላ እሳቤዎች

በሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ ልማድ ስፌትን እግር በሚበዛበት ቦታ ተቀምጦ መስፋት የተከለከለና እንደ ነውር የሚቆጠር ድርጊት ነው። ይኸውም ባለሙያዋን ለክፉ ዐይን አሳልፎ ይሰጣታል ተብሎ ይታመናል። ይህም ከክንድ ቁርጥማት እስከ ሞት ድረስ የሚያደርስ ነው ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን ለዐይን ተጋላጭ ከሆነች ክፉ መንፈስ በእጇ ስለሚገባ ባለሙያዋ የምትሰፋቸው ስፌቶች ውበታቸው ይደበዝዛል፣ ስፌት አያምርላትም ተብሎ ይታመናል።

> አሁን እኔ ይኸው ክንዴን ተይዤ ቀን እግዞ ሌት እግዞ ነው፤ እና ምን ይሉኛል ከዛ አውራ ጎዳና ላይ ሆነሽ እየሰፋሽ እኮነው እስኪ ዞር በይ ይሉኛል። እኔስ ቤቴን ትቼ የት ልሂድ? እንጂ እሱማ ሰለስትና/ከትናንት ወዲያ የሞተችው ልጅ ከሱቋ ሆና ምትሰፋው ሞሰብ ልዩ/ውብ ነበረ፤ ታዲያ ምን ይሆናል የሰው ዐይን አሳልፎ ሰጣት፤ ቡዳ በለጋነቷ ቅርጥፍ አደረጋት፤ (ወ/ሮ ውባለም አማረ፣ ቃ.መ፣ 07/02/2015ዓ.ም፣ ይስማላ ቀበሌ)።

ከቀረበው መረጃ ማኅበረሰቡ ሴቶች በአውራ መንገድ ወይም እግር በሚበዛበት ቦታ ሆነው የስፌት ቁሶችን ማዘጋጀታቸው ለክፉ ዐይን ተጋላጭ ያደርጋቸዋል በሚል እሳቤ ነውሮችን አውጇል። ይህ የነውር እወጃም ከክፉ ዐይን ተጋልጦ በማስጠበቅ የባለሙያዎችን ደህንነት ብሎም የስፌት ቁሶችን ጥራት ከማስጠበቅ አንጻር ግላዊያዊ ተግባር (manifest function) እንዳለው መረጃዎች አመላክተዋል። በሌላ በኩል በሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ ውስጥ ከዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ልማድ አንጻር የስፌት ቁሶችን ማዘጋጀት የሴቶች ተግባር ተደርጎ ይታሰባል። የዚህ እሳቤ አንደኛው ምክንያት ድርጊቱን የጓዳ ሥራ አድርጎ ከመቁጠርና ሴትነትን ከጓዳ ጋር ከሚያስተሳስር ማኅበረሰባዊ እሳቤ የመነጨ ነው። ሴቷ ጓዳ ሆና የስፌት ሥራዋ ላይ የምታተኩር ከሆነ ከሰው ጋር ተግናኝታ አሉባልታ አትሰማም፤ ይህ ደግሞ ትዳርንና ማኅበረሰባዊ መረጋጋትን ይፈጥራል የሚል ከመዋቅራዊ ጠቀሜታዊነት ንድፈሃሳብ እሳቤ ጋር የተቆራኘ የልማድ መሠረት እንዳለ አውዳዊ መረጃዎች አመላክተዋል። በመሆኑም የሰው እግር በሚበዛበት ቦታ ተቀምጦ መስፋትን በተመለከተ ያለው ማኅበረባህላዊ ክልከላ አንድም አውዱ በሚፈጥረው ከሰዎች ጋር የመገናኘት አጋጣሚ ሥራ መፍታት ይከሰታል ብሎ ከመስጋት፤ አንድም ደግሞ በዚህ ምክንያት ከሚፈጠር አሉባልታ በመጠበቅ ማኅበረሰባዊ መረጋጋትን ለማስቀጠል የተፈጠረና የሰረፀ የነውር እሳቤ ነው። ይኸም በማኅበረሰቡ ውስጥ ነውሮች ከተፈጠሩበት ተቀዳሚ ምክንያት ወይም ግላዊያዊ ተግባር ጀርባ ያለውን ኅቡኣዊ ተግባር (latent function) የሚያመላክት ነው።

በሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ የስፌት ቁሶች ዝግጅት ልማድ ውስጥ ገና ያላለቀ/ውጥን ስፌት ላይ ወስፌ ስክቶ መተውና ማሳደር ባለሙያዋን ለደረት ውጋት ያጋልጣል ተብሎ ስለሚታሰብ የተከለከለ ተግባር ነው፤ (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ 29/11/2014ዓ.ም፣ ይስማላ ቀበሌ)። በማኅበረሰቡ ልማድ በስፌት ወቅት ሴቶች ግራምጣ ሰንጥቀው ሲሰፉ ውጥኑ ላይ እየሰፉበት ያለው የግራምጣ ዘለላ ሳያልቅ አቋርጦ የመነሳት ልማድ የላቸውም። እንዲነሱ ግድ የሚሉ ሆነቶች ቢፈጠሩ እንኳን "የጀመርሁትን ልጨርስ ብየ ነው ትንሽ ታገሱኝ" ሲሉ ይሰማሉ። የተጀመረው ግራምጣ ሲያልቅ ወስፌውም ተሰክቶ ሳይሆን ግድግዳ ላይ በጭቃ የሚሠራ የዕቃ መደርደሪያ/ጭነት ላይ እንዲቀመጥ ይደረጋል። ጅምሩ ካላለቀ ግን ውጥኑ ላይ እንዲሰካ ስለሚጋብዝ ይኸ ደግሞ ለደረት ውጋት ይዳርጋል፤ ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም ከዚህ የክፉ ዐይን ተጋላጭነት ለመራቅ ሲባል የተፈጠረው የነውር እሳቤ ወይም ማኅበረባህላዊ ክልከላ የባለሙያዋን ደህንነት ከማስጠበቅ አንጻር ግላዊያዊ ተግባር ያለው ሲሆን በአንጻሩ ማኅበረሰቡ በዚህ የነውር እውጃ ባለሙያዋ ዝርክርክ እንዳትሆንና የስፌት ተግባሩን ቶሎ ከውኖ የተጀመረው ግራምጣ እንዲያልቅና የሥራ ትጋትን በመፍጠር በኩል ሌላ ማኅበራዊ ሚና ወይም ኅቡኣዊ ተግባር እንዳለው መመልከት ተችሏል።

በሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ ውስጥ ገና ጅምር/ውጥን የስፌት ቁሶችን በጭንቅላት መሸከም የተከለከለና እንደነውር የሚቆጠር ነው። ይኸውም የመስፋት ሂደቱን ቶሎ እንዳያልቅ ያደርገዋል፤ ገድን ወይም መልካም አጋጣሚን ያሸሻል ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም ማንኛዋም ሴት እየሰፋች ያለችውን ውጥን እንዳትሸከም ትደረጋለች፤ ይህን ካደረገች ግን ስፌቱ ቶሎ ካለመቋጨቱም ባለፈ እንደ ሰነፍና ችኩል ትቆጠራለች። አንገትን ደፍቶ ሰከን ብሎ መስፋት ነው እንጂ የምን አድርሱኝ/መቸኮል ነው? ተብላ እንደምትወቀስ ይናገራሉ (ወ/ሮ አዘነግ፣ ምልከታና ቃ.መ. 14/02/2015ዓ.ም፣ ይስማላ ቀበሌ)። ይኸም ችኩልነትን ለማስወገድና ሥራ ላይ አተኩሮ መሥራትን

ለማስረጽ የተፈጠረ የነውር እወጃ ወይም ክልከላ ነው። ይህም በተጠኘው ማኅበረሰብ ስከነት/መረጋጋት ለሴቶች የሚሰጥ ማኅበረሰባዊ አረዳድና ሥነልቦናዊ ምስል መሆኑን የሚያመላክት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሴቶች በስፌት ወቅት ሥራቸው ላይ በማተኮር የመስፋት ተግባሩን በአጭር ጊዜ እንዲያጠናቅቁ ለማትጋትና ሌሎች አዘናጊ ነገሮችን እንዳይፈጽሙ ለማቀብ የተጠቀሙት ልማዳዊ ክልከላ ወይም የነውር እሳቤ ነው። የልማድ መሠረተ እሳቤውም በመዋቅራዊ ጠቀሜታዊነት ንድፈሃሳብ እንደተገለጸው የሴትነት ወግን ከማስተማርና ሥራን ከማትጋት የመነጨ እንደሆነ መረጃዎች አመላክተዋል።

### 4.2 ከዕደጥበባት አጠቃቀም ዐውድ ጋር የተያያዙ የነውር እሳቤዎች

በዚህ ክፍል የተቃኙት ነውሮች ማኅበረሰቡ በሚያከብራቸው ልዩ ልዩ የሕይወት ዑደት ሽግግሮች ውስጥ ያለን የዕደጥበባት አጠቃቀም ክልከላ/የነውር እወጃን የተመለከቱ ናቸው። Gennep (1960) የሕይወት ዑደት ሽግግር እንደ ልደት፣ ክርስትና፣ ምርቃት፣ ሰርግ/ጋብቻ፣ ልጅ መውለድ፣ ጡረታ መውጣት፣ ሞትን የመሳሰሉትን ዋና ዋና የማኅበራዊ ደረጃ ሽግግርን (major social status transition) እንደሚጠቀልል ይገልጻሉ። ይሁንና በሰሜን አቸፈር ማኅበረሰብ የዕደጥበባት አጠቃቀም ልማድ ክልከላ ወይም የነውር እወጃ የታየባቸው የሽግግር ዐውዶች የወሊድ፣ የሰርግ፣ የፍቺና የውርስ ዐውዶች ናቸው። ይህ ሲባል የዚህ ጥናት ዓላማ ስለማኅበረሰቡ የሕይወት ዑደት ምዕራፎች አጠቃላይ መረጃ መስጠትና የከዋኔ ሂደቱን የጠበቀ ትንተና ማቅረብ ስላልሆነ በማኅበረሰቡ ልማድ በእነዚህ ዐውዶች የሚታዩ የነውር ወይም የክልከላ እሳቤዎችን ለማሳየት ብቻ ስለ ዐውዱ መጠነኛ መንደርደሪያ ቀርቧል።

#### 4.2.1 በወሊድ ዐውድ ውስጥ የሚታዩ የዕደጥበባት አጠቃቀም ማኅበረባህላዊ ክልከላዎች/የነውር እሳቤዎች

በተጠኘው ማኅበረሰብ ውስጥ በወሊድ ጊዜ የሚታየው የዕደጥበባት አጠቃቀም ልማድ በምጥ ወቅትና በአራስ ቤት ቆይታ የሚፈጸሙ ናቸው። የአራስ ቤት ቆይታ ሲባልም ወላዷ ከተገላገለች በኋላ በማኅበረሰቡ ልማድ መሠረት የአራስ ቤት ቆይታዋን እስከምትጨርስበት ማለትም እስከ ዐሥረኛው ቀን ድረስ በዕደጥበባት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ዖታዊ ክዋኔዎችን የሚመለከት ነው። በዚህም እልልታና አቀባበል[13]፣ ከአልጋ የመውጣት[14] ሥርዓትና የጀርባሽን ይንካው[15]/የጀርባሽ ይክበድ ሥርዓትን ያካትታል። ነገር ግን የዕደጥበባት አጠቃቀም ክልከላ ወይም የነውር እወጃ የታየው የምጥ ወቅት በመሆኑ እሱ ላይ ያተኮረ ትንተና ቀርቧል። በዕደጥበባት አጠቃቀም ዙሪያ ያለው የተጠኘው ማኅበረሰብ ሥርዓተ ዖታዊ ልማድ ሲነሳ ከባለቤትነት መብት አንጻር ያለው የዕደጥበባት አጠቃቀም ለወንድነትና ለሴትነት የተገቡ ወይም "የወንድ ዕቃ" "የሴት ዕቃ" ተብለው

[13] ህጻኑ/ኗ በተወለዱ ወንድ ከሆነ አስራ ሁለት ጊዜ ሴት ከሆነች ዘጠኝ ጊዜ የሚፈጸም የዕልልታ አቀባበል ነው።
[14] አራሷ በሦስተኛ ቀኗ ከመሬት መኝታ ወደ አልጋ መኝታ እንድትሸጋገር የሚፈጸምላት ሥርዓት ነው።
[15] ህጻን በተወለደ በሰባተኛው ቀን የሚፈጸም ሥርዓት

የተለዩ ናቸው። ይኸውም በእርሻ ቁሶችና እንደ ጀንዲ[16]፣ ላምነት[17]፣ አጎዛ[18] ዓይነት የቆዳ ምንጣፎች እንዲሁም እንደ አቆማዳ[19]ና የሰሌን ሻንጣ[20] በወንዱ ቁጥጥር ሥር ያሉና እሱ የሚያዝባቸው ናቸው። በአንጻሩ እንደ ስፌት ቁሶችና የጓዳ እቃዎች ደግሞ በሴቷ ቁጥጥር ሥር ያሉና የሴት እቃ ተብለው የተፈረጁ ናቸው። ታዲያ እነዚህ "የሴት ዕቃ" ተብለው የተለዩት ዕደጥበባት ሴቷ በዘወትራዊ ተግባሯ ከምትገለገልባቸው ባለፈ በጭንቅና በጣር ውስጥ ስትሆን ከጭንቀቷ እንድትገላገል አማላጅ የመሆን እና እንደ ጥሩ ገድ አምጪ/ምልኪ የመሆን ኃይል እንዳላቸው ተደርጎ ይታመናል። ለዚህ ደግሞ የሚጠቅሱት የመጀመሪያው ምክንያት የሴት ልጅ ውቃቤ ወይም ቆሌ ማጀት ባሉ የሴት ዕቃዎች ላይ ያረፈ ነው፤ ብለው ከማሰብና እነዚህ ዕቃዎች ሲከፈቱ ቆሌዋ ታስታርቃለች፤ የወላዷ ማሕፀን ይከፈታል፤ እመአምላክም ትመጣለች ብሎ ከማመን ጋር የተያያዘ እንደሆነ መረጃ አቀባዮች ይገልጻሉ።

ኹለተኛው ደግሞ ሴትነትንና ቆሌን/ውቃቢን አቆራኝቶ መመልከት ነው። በማኅበረሰቡ አመለካከት ሴቶችን ከቆሌና ከባለውቃቢነት ጋር አስተሳስሮ የመመልከት ልማድ አለ። ይህንም ሴት ምታዘው በማጀቷ ነው አድባሯም ቆሌዋም በማጀቷ ቅርቧ ናት ብለው ያስባሉ፤ ስትለብስ ስታጊጥ ውቃቢ ይቀርባታል፤ በሴት እቃዎች ላይ ጌጣጌጦችን ስታደርግ የበረከት ቆሌ እንዲያርፍ ታደርጋለች፤ ወንድ ልጅ ማጀት ከገባ የማጀት ቆሌዋ አትወድም፤ ሴት ልጅ ቆሌን የመለማመን፣ የማማለድና የማቋደስ ጥበብ አላት፤ ብለው ያምናሉ። ይህ ሴትን ከቆሌ ጋር በተለይም ከማጀት አድባሯ ጋር ያስተሳሰራትን ነገር ሲገልጹም የሚያነሱት አፈታሪክ አለ። ይኸውም በሜዳ ያለው የወንድ ቆሌ በፈረንጆች ተጠልፎ ከሃገር ሲወጣ ማጀት ያለችውን እንስት ቆሌ ግን ስላላገኟት ከዛው ከጓዳ ቀርታ ሲለማመኗት እንደሚኖሩ ከሚጠቅሱት አፈታሪክ ጋር የተያያዘ ነው።

> ...ለምንድን ነው ቆሌ ከሴት ጋር ምትያያዘው፤ በደርግ ጊዜ ይሁን ከዛ በፊት ብቻ ድሮ ነው በወንዝ ላይ በትላልቅ ዛፍ ላይ ያሉ ተላላፊዎችን/ቆሌዎችን የሚጠልፍ ፈረንጅ መጣ ይባላል። መንግስት ተክኖለጅ ሊሠራ አምጡ ብሏቸው እነዛን ወስዶ ለእሱ ማጂክ አረጋቸው፤ ምንድነው የሠራ ማጂክ ሲሠራ? የሞተር ማንቀሳቀሻ እ..መብራት ወፍጮ ሚሠራ በምን ላይ ነው ከዛ ባሻገር ስልክ በምን ነው ሚነጋገር? እነዚህ ተጠልፈው ነው። ጠላፊው በማግኜት ያን ጠላልፎ ወሰደ ሻምብላ[21] አካባቢ ፈረንጁ ከደብረሲና ጅን ጠልፎ ሲሄድ መንገድ ላይ የቆየ አብሮ አደግ ዛር ያለበትን ሰው ሲያገኝ 'አምባዬ ወልዴ ኧረ ባክህ አስቀረኝ ጠልፎ ወሰደኝ' ብሎ ጮኸ ይባላል። አንዱ ሳይገኝ በለስን ተሻገረ፤ እና ወንዱ ጅን ተጠልፏል ይባላል። አባይና ጣና

---

16 ከከብትበቆዳ የሚዘጋጅ ጸጉር አልባ ምንጣፍ

17 ከከብት ቆዳ የሚዘጋጅ ባለጸጉር ምንጣፍ

18 ከፍየል ቆዳ የሚዘጋጅ ባለጸጉር ምንጣፍ

19 ከቆዳ የሚዘጋጅ የእህል መያዣ ከረጢት

20 ከሰሌን የሚዘጋጅ የልብስ ሻንጣ

21 ሻምብላ ሰሜን አቸፈር ወረዳ ውስጥ የሚገኝ የገጠር ቀበሌ ነው።

> ሲገናኝና ሲነካካ ለሀገር ሰይጣን ይወርዳል፤ ቀንድ ያለው ጅን ይገለጣል መቅሰፍት ያወርዳል ይባላል። ዛሬ ረድኤቱ ሸሽ ሚባል ይህ ተጠልፎ ነው። ከራስ ጸጉር ሲነጭ ራስ አያምም? ምንድን ነው? ላበት አይል ሚሆን፤ ለምን? ጥላ የነበረው አለቀ። እንስቷ ግን ማጀት ናት፤ እንዳንዷም ወንዝ ላይ ታድራለች፤ አለች ጠባቂ ናት፤ በተለይ ለሴት ትራራለች፤ (አቶ ካሴ አንዳርጌ፣ ቃ.መ.፣ 29/11/2014ዓ.ም፣ ይብሊተረፊት ቀበሌ)።

በማለት የገለጹ ሲሆን ማጀት የሚቀመጡ የሴት ዕቃዎች በረከትና ረድኤት እንዲቀርባቸው ይህች ሴት ቆሌ እንድትጠጋቸው ያደርጋሉ፤ በምጥ ጊዜ ሲከፋፈቱም ወላዷን ውቃቢ ቀርቧት ማሕፀኗ ይከፈታል፤ ብሎ ከማመን ጋር የተያያዘ እንድምታ እንዳለው መረጃዎች አመላክተዋል። ይህ ድርጊታዊ የነውር እሳቤ ከገድ ጋር በተያያዘ ባለ ተቀዳሚ አመክንዮ የተፈጠረ እንደሆነ መረጃዎች ያመላከቱ ቢሆንም ከዚህ እሳቤ ባለፈ ሴትነት በጓዳ የተወሰነ፣ በጓዳ የሚዳኝና የሚማለድ ተደርጎ የሚታሰብበትን ማኅበረሰባዊ እሳቤ ከማስረጽ ጋር የተያያዘ ኀቡኣዊ ተግባር እንዳለው መረዳት ተችሏል።

በዚህ አውድ የታዩ የዕደጥበባት አጠቃቀም ክልከላዎች ወይም የነውር እወጃዎች ገድን ያርቃሉ ከሚል እሳቤ የመነጩ ናቸው። በማኅበረሰቡ ልማድ መሠረት በምጥ ጊዜ ጓዳ ያሉ የሴት እቃዎችን ማለትም ጎታ፣ ጉሽጉሻ፣ አገልግል፣ የእንጀራ ሞሰብ፣ የቡሆ ዕቃ፣ የጨው ማድጋ፣ የቅቤ ቅል፣ ጋን...ሁሉ ከድኖ ማስቀመጥ የወላዷን ማሕፀን እንዳይከፈት በማድረግ ቶሎ እንዳትገላገል ያደርጋል/የምጥ ስቃይዋን ያረዝማል ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም በምጥ ወቅት እነዚህ ቁሶች ተከድነው እንዲቀመጡ አይፈቀድም።

> ሴት ስትወልድ ምጥ ስትያዝ ምጡ እንዳይጠብቅባት የሴት እቃ ይከፈታል፤ ጋኑ የተለጎመው አገልግል ሲከፈት አድባሯም ትለማመናለች፤ እመአምላክ ትመጣለች። ጋን ተመርጎ እንደሆነ ይከፈታል፤ ማሕፀኗ እንዲከፈት ስትገላገል ገና ያው የደስደስ ነው እልልታ ለሴቷ ዘጠኝ ጊዜ ለወንዱ ደሞ አስራሁለት ጊዜ ይባላል" (እማሆይ ዓየሁ ሻረው፣ ቃ.መ. 21/12/2014ዓ.ም፣ ኳላ ባካ ቀበሌ)።

ማኅበረሰቡ በተዘጋ ነገር ምንም አይገባም፤ ረድዔት/በረከት አይገባም፤ ምሕረት አይገባም፤ የተቋጠረ ነገር ተስፋ አይሰጥም ፈታ ሲሉ ሲስቁ ሲጫወቱ መልካም መንፈስ ይቀርባል፤ የተቋጠረው ሲፈታ የተከደነ ሲከፈት ምጥ አይጠብቅም፤ ማሕፀን ይከፈታል ብሎ ያምናል። በመሆኑም እነዚህ ቁሶች በምጥ ጊዜ ተከድነው መቀመጥ እንደሌለባቸው ይገልጻሉ። ከዚህ በተጨማሪም እቃዎች ሲከፈቱ በእነሱ ላይ ያደረችው የሴት ቆሌ ስለምትለማመንላት ምጧ አይጠብቅም ብለው ያምናሉ። ይህ የሴት ዕቃዎችን ተከድኖ እንዳይቀመጡ የሚከለክለው ማኅበረባህላዊ እሳቤ ገድን ከማቅረብና ምጥን ከማቅለል አንጻር ተቀዳሚ ተግባር እንዳላው መረጃዎች አመላክተዋል። ከዚህ ጀርባ ደግሞ በሴቶች የሚዘጋጁ ዕደጥበባት ከዘወትራዊ አገልግሎታቸው ባለፈ ልዩ ሃይል ያላቸው ተደርገው እንዲታሰቡ በማድረግ ሴት ልጅ ለሴትነት የተገቡ ዕደጥበባትን ማዘጋጀት አለባት የሚለውን

ማኅበረሰባዊ ደንብ ከማስረጽና ሴቷም እነዚህ ዕደጥበባት በጭንቋ ጊዜ መማጸኛዎቿ እንደሆኑ ቆጥራ ማኅበረሰባዊ የሴትነት ደንቡን አሜን ብላ እንድትቀበል ከማድረግ አኳያ ኅቡኣዊ ተግባር እንዳለው መረዳት የተቻለ ሲሆን ይህም በተጠኘው ማኅበረሰብ ውስጥ የነውር እሳቤው የተፈጠረበትን ማኅበረባህላዊ አመክንዮ የሚያመላክት ነው።

### 4.2.2 በጋብቻና በሰርግ ዐውድ የሚታዩ ከዕደጥበባት አጠቃቀም ጋር የተያያዙ የነውር እሳቤዎች

በሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ የጋብቻ ልማድ ውስጥ የማደጎ፣ የጋለሞታና የተከርቸም/ተንከባለል የሚባሉ የጋብቻ ሥርዓቶች አሉ። በማኅበረሰቡ የጋብቻ ልማድ ውስጥ የማደጎ ጋብቻ ሲባል የመጀመሪያ ባልና ሚስት ሆነው የሚጋቡበትና ሙሽሪትና ሙሽራው ከተጋቡ በኋላ ለአካለመጠን ደርሰው ጎጆ እስኪወጡ ድረስ ሙሽሪት ከእናትና ከአማት ቤት በምልልሾ እንድትቆይ፣ እንድታድግና ለጎጆ የሚያበቋትን ሙያዎች እንድትማር የሚደረግበት ጋብቻ ነው። ኹለተኛው የጋብቻ ዓይነት የጋለሞታ ጋብቻ ይባላል። ይኸውም ወንዱም ሆነ ሴቷ ከዚህ ቀደም ከሌላ ሰው ጋር ጋብቻ ፈጽመው ቆይተው በአጋጣሚዎች ምክንያት ቢለያዩና ድጋሜ ሌላ ጋብቻ ቢፈጽሙ ሥርዓቱ የጋለሞታ ጋብቻ ይባላል። ሦስተኛው የተከርቸም ጋብቻ ሲሆን ወንዶች ወደ ሴቶች መኖሪያ ቀዬ በመግባት የሚፈጽሙት ሲሆን በማኅበረሰቡ ዘንድ በበጎ ዓይን አይታይም። ምክንያቱም የሴት ሀገሯ የባል ሀገር ነው ስለሚባል ሴት እንጂ ወደ ባል ሀገር መሄድ ያለባት ወንድ ወደ ሚስት ሀገር ሂዶ መግባት የለበትም፤ የሚል አቋም ስላላቸው ነው። ከዚህም የተነሳ በተለያዩ ምክንያቶች "ተከርቸም" ሂዶ የገባ ወንድ ቢገኝ "ተንከባለል" ተብሎ ይሰደባል፤ በረባው ባረባውም ነገር በአሽሙር ይሰደባል።

ታዲያ በእነዚህ የጋብቻ ሥርዓቶች ውስጥ ከዕደጥበባት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ለሴቷም ሆነ ለወንዱ የሚፈጸሙ ሥርዓቶች የተለያዩ መሆናቸውን ከመረጃዎች ማወቅ ተችሏል። ይሁንና የዕደጥበባት አጠቃቀምን በተመለከተ የነውር እወጃ ወይም ክልከላ የታየበት የማደጎ ጋብቻ ሥርዓት በመሆኑ እሱ ላይ ትኩረት ተደርጓል። በማኅበረሰቡ የማደጎ ጋብቻ ሥርዓት ውስጥ የመተጫጨት ሥርዓት፣ የሰርግ፣ የመጋረድ፣ የምርቃትና ስም የማውጣት፣ የምልልሾ እና የጎጆ መውጣት ሥርዓቶች አሉ። በመሆኑም እነዚህ ሥርዓቶች ከእነሙሉ ክዋኔያቸው ማቅረብ የዚህ ጥናት ትኩረት ባይሆንም እንኳን ከዕደጥበባት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ያለውን ልማድ ለመጠቆምና ወደ ነውር/ክልከላ እወጃው ለመንደርደርያነት የሚያስፈልጉትን ለመጠቆም ተሞክሯል።

የትዳር አጋርን ከማግኘት ጋር በተያያዘ ያለው የዕደጥበባት አዘገጃጀት መለኪያ "መፍተልና መስፋት ትችላለች?" የሚለው እንደሆነ ከመረጃዎች ማወቅ ተችሏል። በመሆኑም ሴትን ልጅ ወደ ባለትዳርነት የሚያሸጋግራት የመታጨት እርከን ላይ ለመድረስ እንደመስፈርት እሷ እንኳን ልጅ ብትሆን ወይም የማደጎ ጋብቻ ከሆነ የእናት የስፌትና የፈትል ሙያ ይጠየቃል። ከእናት ቤት ተገብቶ ግድግዳ ላይ የስፌት ዕቃዎች ተደራርበው መሰቀላቸው፣ ባል ሲወጣ ጋቢ ከኩታ አቀያይሮ መልበሱ፣ ሚስትም ቀሚስ ከኩታ አቀያይራ መልበሷ፣ ደጋንና እንዝርት ስታጮህ መሰማቷ ሁሉ ይታያል፤ ይጠየቃል።

በሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ ሰርግ ሲታሰብ እንደ ሙዳይ፣ ዋንጫና ቁኒ ቅል[22] የተባሉ ዕደጥበባትን ማዘጋጀት የተለመደ ነው። እነዚህ ዕደጥበባት የተለያዩ ማኅበራዊና ባህላዊ ክዋኔዎች የሚፈጸሙባቸው ናቸው። ሙዳይ በሙሽራ ወግ የሴት መሣሪያ የሚባሉት እንደ ወስፌ፣ እንዝርት ያሉትና እንደ ኩል፣ መስታውት፣ ስንቡል የመሳሰሉ መዋቢያዎች የሚሄዱባት የስፌት ቁስ ናት። በሙዳዩ ውስጥ ወስፌና እንዝርት መከተቱ ሙሽሪት ማደጎ ብትሆንና ዕለት መስፋትና መፍተል ባትችል እንኳን መስፋትና መፍተል የሴትነት ወግሽ፤ የእናት ደንብሽ ነው፤ ለማለት ሲሆን በምልልሾ ወቅትም እንድትለማመድባቸው ይደረጋል።

ቁኒ ቅል ሙሽሪት ከአማቶቿ ቤት ስትሄድ ራሷን የምታስውበት በስንቡል የተለወሰ ቅቤ ይዛበት የምትሄድበት ነው። በሙሽራዋ ሙዳይ ውስጥ የሚከተቱ የመዋቢያ ዕቃዎች ኩል፣ መስታወት፣ ሚዶ (የጸጉር ማበጠሪያ) ሲሆኑ በተለይ ሳዱሌ መስታወትና ሚዶ የሚሄዱበት ምክንያት ሙሽሪት ወደፊት ከምትደርሳባቸው የሕይወት ዑደት ምዕራፎች ጋር የተያያዘ ተግባር እንዳላቸው ወ/ሮ አዘነግ፣ ቃ.መ.፣ 02/11/2014ዓ.ም፣ ይስማላ ቀበሌ) ገልጸዋል። ይኸውም መስታወቱ ፈቷን ለማስዋብ ከምትገለገልበት ባለፈ የማደጎ ጋብቻ ዙርጋሜ[23] ሆና ካገባች በኋላ ቀጣይ የምትሸጋገርበት የእድሜ ደረጃ ሳዱላ[24] ነው፤ በመሆኑም ጸጉሯን ሳዱላ ስትላጭ ከአናቷ ወረድ ብሎ በብር ቅጥል ወይም በሳዱሌ መስታወት ተለክቶ ተቀንብቦ ይላጫል። በዚህ ተግባሯም መስታወቷ ሳዱሌ የሚል ተቀጣይ ስያሜ እንደተሰጣት ይናገራሉ። ከዚህም የተነሳ እናት የሙሽሪት ሙዳይ ውስጥ ሳዱሌ መስታወት ከታ ስትልካት ከዚህ ቀጥሎ የምትሸጋገሪበት የእድሜ እርከን የሳዱሌነት ዘመን ነው ስትልም ጭምር ነው። ሚዶ የሚሄደው ደግሞ ከሳዱሌነት ቀጥሎ የሚመጣው የእድሜ እርከን ጎፈሬነት ስለሆነ ይህን ለማመላከት እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። ስለሆነም እነዚህን አሟልታ ያልላከች እናት እንደምትነወርና ሙሽሪትም "ምን ዓይነት እናት አሳድጋሽ ነው?" ተብላ ክብሯ ዝቅ ተደርጎ እንደሚታይና እንደምትተች እማማ[25] አትክልት የተባሉ መረጃ አቀባይ ገልጸዋል (ቃ.መ. 22/10/2014፣ ይስማላ ጃንኪት ቀበሌ)።

እነዚህ ከእናት የተበረከቱ የሙሽራ ደንብ ዕቃዎች ከሙሽሪት ጋር አብረው ከሄዱ በኋላ በስር ሚዜው አማካኝነት አማት እንድትረከብ ይደረጋል። ይህ የሚሆነውም በተለያዩ ምክንያቶች ትዳሩ አልሰምር ቢል አላቂ ያልሆኑት የሴት ዕቃዎች ለሙሽሪት መመለስ ስላለባቸው አጋጣሚ ቢጠፉ ወይም እናት ሳትልክ ብትቀር እንኳን አማት ቀምታ አስቀረች፤ ተብላ እንዳትነወር መሆኑን ከላይ የቀረበው መረጃ ያሳያል። ይህም እነዚህ እቃዎች ከማኅበረሰቡ የሴትነት እሳቤ ጋር ያላቸውን ቁርኝት የሚጠቁም ነው። ይኸውም ማኅበረሰቡ ሴት ልጅ ትዳር መሥርታ ስትኖር በሴት ደንብ ቤቷ ውስጥ ተቀምጣ መስፋትና መፍተል አለባት፤ ይህም ከወሬና አሉባልታ እንድትታቀብ ስለሚያደርግ የተረጋጋ ትዳርና ማኅበራዊ ደህንነት እንዲሰፍን ያደርጋል የሚል እሳቤ አለው። ታዲያ

---

[22] ሙሽሪት በሰርጓ ቀን የጸጉር ቅቤ የምትወስድባት አነስተኛ ቅል

[23] በማኅበረሰቡ ልማድ የሴትን ልጀጅ የዕድሜ ሽግግር የሚያመለክት የጸጉር ቁርጥ ዓይነት ሲሆን ከሕጻንነት ወይም ከተሪ ቁረርጥ በኋላ የሚመጣ ነው ብዙ ጊዜ ሴቶች በዚህ ጊዜ ለማደጎ ጋብቻ የደረሱ ተደርጎ ይታሰበባል

[24]ከዙር ጋሜ በኋላ የሚቆረጡት ሲሆን አግብታ ለጎጆ ስትደርስ የምትቆረጠው ነው።ከጭንቅላቷ በኋላ በኩል በብርቅጥል/ማርትሬዛ ወይም በሳዱሌ መስታውት ተለክቶ ክብ መላጣ ይወጣላታል።

[25] በማኅበረሰቡ ውስጥ በእድሜ የገፉ ሴቶችን ለመጥራት የሚጠቀሙት ስያሜ ነው

ይህን የሴትነት እሳቤ የማስረጽ ተግባሩ የሚጀምረው በሰርግ ቀን በሚሰጧት ዕደጥበባት የሴትነት ወጓንም እንድትቀበል በማድረግ ነው። እነዚህን የሴት ደንብ ዕቃዎች በሰርግ ቀን አለመውሰድ እንደነውር የተቆጠረበት ምክንያትም በትዳር ውስጥ ያለውን የሴትነት እሳቤ ለማስረጽ መሠረት የሚጣሉበት አጋጣሚ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ እንደሆነ መረጃዎች አመላክተዋል።




ከግራ ወደ ቀኝ የማደጎ ሙሽራ በሰርጓ ቀን የምትወስዳቸው የቅቤ መያዣ ቁኒቅል፣ ሙዳይና የሙሽሪት መጠጫ ዋንጫን በቅደም ተከተል የሚያሳይ ምስል፤ በአጥኚዋ የተነሳ ፎቶ (03/13/20!4ዓ.ም፣ ይስማላ ቀበሌ እና 21/12/2014ዓ.ም፣ ኳላባካ ቀበሌ))

የሙሽራ ዋንጫ ሙሽሪት በሰርጓ ቀን ወደ ባሏ ቤተሰብ ስትሄድ ከእናቷ የምትበረከትላትና ከአማቶቿ ቤት ስትጋረድ ወይም በመጋረድ ሥርዓት ስትቆይ የምትጠጣባት ሲሆን ከሴትነት ክብር ጋራ የተያያዘ እንድምታ አላት። መጋረድ መሽሪት በሰርጓ ቀን ወደ ባሏ ቤተሰቦች እንደሄደች በቀጥታ ከቤተሰቡ ጋር አትቀላቀልም። በሦስተኛው ቀን ተመርቃና የሥም ማውጣት ሥነሥርዓት ተፈጽሞላት እስክትቀላቀል ድረስ ሚዜዎች ተራ በተራ ጋቢያቸውን እየጋረዱ እንደ ጫጉላ ቤት በዚያ እንዲቆዩ ይደረጋል። ስትበላም ሆነ ስትጠጣ አትታይም፤ ዋንጫዋን የምትጠቀምባትም በዚህ ወቅት ነው። የሙሽሪት ዋንጫ የንጽሕናዋ ምሳሌ ስትሆን እናት በልጇ የሰርግ ቀን ይህችን ዋንጫ ስትሰጣትና ሙሽሪት ወደ ባሏ ቤተሰቦች ይዛ እንድትሄድ ሲደረግ "ልጄን የሰጠሁህ እስከ ክብረንጽሕናዋ ነው" የሚል እንድምታ እንዳለው መረጃ አቀባዮች ተናግረዋል፤ (አቶ መንበር፣ ቃ.መ.፣ 23/10/2014ዓ.ም፣ ይብሊተረፊት ቀበሌ)።

ከመረጃው በማኅበረሰቡ ልማድ ዋንጫ የንጽህና ተምሳሌት ተደርጋ እንደምትታሰብ መረዳት ተችሏል። ይህ ከጽዋ ጋር በተያያዘ ያለው የንጽህና እሳቤ በተለያዩ ሀገራት ባህል፣ የክብረበዓልና ሃይማኖታዊ ሥነሥርዓቶች ውስጥ የሚታይ ነው። በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ጽዋ የሴትነትና የመራቢያ አካል ትእምርት ተደርጎ ይታሰባል። በአንዳንድ የሕይወት ምዕራፍ አውድ ውስጥ ጽዋና

ቢላ በአንድነት የሴትነትና የወንድነትን ጥምረት እንደሚወክሉ ይገለጻል። የጽዋ ቅርጽና ተግባሩ የሴትን ልጅ አካል/ማሕፀንና ማኅደረ ሕይወትነት የሚወክል ትእምርታዊ ፍች ይሰጠዋል። በክርስትና አስተምህሮ ጽዋ ለሥርዓተቁርባን መፈጸሚያነት የሚውልና ደመክርስቶስ የሚቀርብበት ሲሆን በመለኮት ጸጋ የከበረ ንዋየ ቅዱስ እንደሆነ (Zarzo 2024, 139-140) ገልጸዋል። በሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ የልማድ እሳቤ ዋንጫ ለሴት ልጅ ክብረንጽሕና ትእምርት ተደርጎ ይታሰባል። በማኅበረሰቡ ዋንጫ የክብር መግለጫ ቁስ ነው። ቤታቸው ለመጣ እንግዳ ክብር ሲሉ በዋንጫ ጠላ ይሰጣሉ። ይህ ከክብርና ከንጽሕና ጋራ የተያያዘው እሳቤ በጋብቻ ሥነሥርዓታቸው ለሙሽሪት በሚሰጥ ዋንጫ ትእምርትነት የሚገለጽ ሆኖ ተገኝቷል።

በማኅበረሰቡ የጋብቻ ሥርዓት መሠረት ሙሽሪት ከእናቷ የምትበረከትላትና በመጋረድ ሥርዓት ውስጥ ስትቆይ የምትጠጣባትን ዋንጫ በአደባባይ መጠቀምም ሆነ ዋንጫዋን መስበር እንደነውር ይቆጠራል። ምክንያቱም ዋንጫዋ ሙሽሪት የማደጎ[26] ጋብቻ የፈጸመች ከሆነች ከነክብሯ መቆየቷን የምትገልጽና ከሰርጉ በኋላ ለአቅመሔዋን ደርሳ ጎጆ እስክትወጣ ድረስ ከነክብረንጽሕናዋ መቆየቷን የምታስመሰክርባት መሆኑን (አቶ መንበር፣ ቃ.መ.፣ 23/10/2014ዓ.ም፣ ይብሊ ተረፊት ቀበሌ) ገልጸዋል። በመሆኑም ከሰርጉ ሥርዓት በኋላ ባሉ ማኅበራዊ ሁነቶች ዋንጫዋን በግላጭ መጠቀምና መስበር ወይም ማጥፋት ክብሯን በአደባባይ እንደጣለች ይቆጠራል። ምክንያቱም ሴት ልጅ ክብሯን ጠብቃ መኖር አለባት፤ በአደባባይ ተገላልጣ መቅረብና እዩኝ እዩኝ ማለት የለባትም ተብሎ ስለሚታመን ይህን ድርጊት ከፈጸመች በማኅበረሰቡ ዘንድ ዝቅ ያለ ግምት ይሰጣታል።

> ሙሽሪት በምትጋረድበት ጊዜ (ጫጉላ ቤት በምትገባበት ጊዜ) ዋንጫ ይዛ ትሄዳለች። ብልህ የሆነች ሴት እችማ ወጋወጌ ናት (የክብሬ መገለጫ፣ ወግማዕረጌ ናት ብላ) ጎጆ ስትወጣ ከቤቷ ታስቀምጣታለች፤ ጠንቃቃ ካልሆነች ግን በዛው በጫጉላ ቤትም ወድቆ ሊሰበር ይችላል። ጠንቃቃዋ ሴት ግን ከፍ ያለ አገልግል ሰፍታ ከማጓ ጋር ታስቀምጣለች እንጂ ሁል ጊዜ አትጠጣበትም፤ ክብሯና ወጓ ስለሆነች በአገልግሏ ታስቀምጣታለች፤ (አቶ ካሤ፣ ቃመ. 29/11/2014ዓ.ም፣ ይብሊ ተረፊት ቀበሌ)።

የቀረቡት መረጃዎች የሙሽሪት ዋንጫ ተምሳሌትነቷ ለክብረንጽሕናዋ ከመሆኑ የተነሳ ማኅበረሰቡ ደግሞ የሴት ልጅ ንጽሕናዋ/ክብሯ በአደባባይ መውጣት/መጉደፍ የለበትም ብሎ ስለሚያምን ይህን ማኅበረሰባዊ እምነት ለመጠበቅ ሲባል የተጠቀሰውን የአጠቃቀም እገዳ መጣሉን የሚጠቁሙ ናቸው። በሌላ በኩል ሙሽሪት ከመጋረድ እንደወጣች በሰው ሁሉ ፊት በዋንጫዋ ባትጠጣም በምልልሾ ወደ እናቷ ቤት ስትሄድ ግን ይዛት እንድትሄድ ይደረጋል። ይህም ሙሽሪት ገና ማደጎ ስለሆነችና ለአካለ መጠን ሰላልደረሰች ለዚህ በቅታ ጎጆ እስክትወጣ ድረስ ከባሏ ጋር ምንም ዓይነት ፆታዊ ግንኙነት እንድትፈጽም አይፈቀድም። ባል ቢፈልግ እንኳን አማቶች የመጠበቅና ለሙሽሪት ወላጆች የገቡትን ቃል የመፈጸም ግዴታ አለባቸው። በመሆኑም ምልልሾ በሄደች ቁጥር ዋንጫዋን

[26] የመጀመሪያ ጋብቻዋን የፈጸመችና ለአቅመ ሔዋን ደርሳ ጎጆ እስከምትመሠርት ድረስ ከእናትና ከአማት ቤት እየተመላለሰች እንድታድግና የሴትነት ወግ እንድትይዝ የሚደረግበት የጋብቻ ሥርዓት ነው።

ይዛ ከሄደች እናት ልጇ ለአካለመጠን እስክትድረስ ድረስ እየተጠበቀች መሆኗንና ከነክብሯ መቆየቷን እንዲሁም አማቶችም ሙሽሪትን ለመጠበቅ የገቡትን ቃል ያከበሩ መሆናቸውን ታውቃለች። ጎጆ ከወጣችና ከባሏ ጋር ግንኙነት ከፈጸመች በኋላ ግን ምልልሾ ብትሄድም ዋንጫ ይዛ እንድትሄድ አይደረግም።

### 4.2.3 በፍቺ ዐውድ የሚታዩ የዕደጥበባት አጠቃቀም ክልከላዎች/የነውር እሳቤዎች

ሌላኛው ከክብር ጋር የተያያዘው የማኅበረሰቡ የነውር እሳቤ በፍቺ ጊዜ ሙሽሪት በሰርጓ ጊዜ ወደ ባሏ ቤተሰቦች ይዛቸው የሄደቻቸውን የሙሽራ ደንብ እቃዎች ቀምቶ ማስቀረት ነው። በማኅበረሰቡ የጋብቻ ልማድ መሠረት ሙሽሪት በተለይም ለአቅመ ሔዋን ሳትደርስ ካገባችና ጎጆ ለመውጣት እስክትደርስ ድረስ ከእናትና ከአማት ቤት ሙያ እየተማረች እንድታድግ የምትደረግ ከሆነ ወይም የማደጎ ሙሽራ ከሆነች ቀደም ሲል የተገለጹትንና ከእናቷ የሚበረከቱላትን እንደ ሙዳይ፣ ቁኒቅል/የቅቤ ቅል፣ ዋንጫ፣ ሚዶ፣ ሳዱሌ መስታወት፣ ወስፌ… ዓይነት የሙሽራ ደንብ ዕቃዎች ይዛ እንድትሄድ ይደረጋል። እነኚህም ከሙሽሪት የዕድሜ ሽግግር ደረጃዎች[27] ጋር ግንኙነት ያላቸው ቁሶች ይዛ ትሄዳለች። ታዲያ በተለያዩ ምክንያቶች ትዳሩ አልሰምር ብሎ ወደ ፍቺ የሚያመራበት ሁኔት ከተከሰተ እነዚህ ቁሶች አማት ቤት እንዲቀሩ አይፈቀድም።

ይህን ደንብ ተላልፋ የሙሽሪትን የወግ እቃዎች ቀምታ ያስቀረች አማት ብትኖር ግን በማኅበረሰቡ ዘንድ የምትነወር መሆኑን "ሙሽሪት ብትፋታ እንኳን የወሰደችውን የሴት እቃ ያስቀረች አማት ውሻ ናት ትነወራለች፤ ደሞ የልጅ ሚስት እቃ እናት የሰጠችው እቃ ይቀማል? ይባላል" (እማሆይ ዓየሁ ሻረው፣ ቃ.መ.፣ 21/12/2014፣ ኳላባካ ቀበሌ) በማለት ገልጸዋል። ከዚህ በተጨማሪም ሙሽሪት በምልልሾ ወቅት ለጎጆ መውጫዋ ከእናቷ ቤት የሰፋቻቸውን እንደ ቀለምሻሽ[28]፣ ሰፌድ፣ ወራንታ[29]፣ ቁና፣ መሳቢያ/ለጠብ፣ አገልግል…ዓይነት ዕደጥበባትን ባል እንዲካፈል አይፈቀድም። በተመሳሳይ ሴቷም እንደ ሞፈር፣ ቀንበር፣ እርፍ፣ ምሳር/መጥረቢያ…ዓይነት የወንድ እቃዎችን እንድትካፈል አይፈቀድም። እሷም የእናቷን እሱም የአባቱን ይውሰድ ይባላል፤ ከዚህ ከተላለፉ ግን ወግ አፍራሽ ተብለው እንደሚነወሩ ወ/ሮ አዘነግ የተባሉ መረጃ አቀባይ ገልጸዋል፤ (ቃ.መ. 02/11/2014ዓ.ም፣ ይስማላ ቀበሌ)። የነውሩ ምክንያትም በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን ሥርዓተፆታዊ እሳቤ ለማስረጽ የተፈጠረ እንደሆነ መረዳት ተችሏል። ይኸውም ሴቷ እንድትወስድ የሚፈቅዱ ቁሶች በእሷ የሚዘጋጁ፣ በአብዛኛው ጓዳ ውስጥ የሚዘጋጁና አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። በአንጻሩ ወንዱ እንዲወስድ የተገቡት ደግሞ በእሱ የሚዘጋጁና ውጭ ላይ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። ይህም ሴትነትን ከጓዳ ወንድነትን ደግሞ ከአደባባይ ጋራ አያይዞ የመመልከት

[27] ቁንጣይቱ ስትዳር ዞር ጋሜ ነው ምትሆን ከፍ ያለችው ስትሆን ሳዱላ ስትዳር ዞር ጋሜ የሆነች መስታውቷና ብርቅጥሏ ለሳድሏ ማውጫ እንድትሆናት አብራ ትሄዳለች። ከዛ ጎፈሬ ትሆናለች ሚዶውም ሚሰጣት ጎፈሬ ስትሆን እንድትነቅስበት ነው። ስንቡሉ ተደቁሶ በብልቃጥ፣ ቅቤው ደግሞ በቁኒ ቅል፣ ሙዳዩም በከረጢት ተጠራቅሞ አንድ ላይ ስር ሚዜው ይዞ ይሄዳል፤ (እማሆይ ዓየሁ፣ ቃ.መ. 21/12/2014ዓ.ም፣ ኳላ ባካ ቀበሌ)።

[28] ከስር ማስቀመጫ/እግር ያላት በማኅበረሰቡ ለቆሎ ወይም ዳቦ ማቀረቢያ የምታገለግል ከግራምጣ ወይም ከክር የምትዘጋጅ የስፌት ቁስ

[29] በማኅበረሰቡ ባህል በአራስጥዬቃ፣ በሰርግ፣ በተዝካርና በማኅበር ወቅት እንጀራ የሚወስዱበት ከቁና ከፍ ያለ የስፌት ቁስ

ማኅበረሰባዊ እሳቤ መኖርን አመላካች ነው። በመሆኑም በዘወትራዊም ሆነ በሕይወት ምዕራፍ ሽግግር ባለው የዕደጥበባት አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ ይኸን ሥርዓተፆታዊ እሳቤ ለማስረጽ ሲሉ የተፈጠረ የነውር እሳቤ እንደሆነ መረዳ ተችሏል።

### 4.2.4 በውርስ ዐውድ የሚታዩ የዕደጥበባት አጠቃቀም ክልከላዎች/የነውር እሳቤዎች

ከክብር ጋር በተያያዘ የሚጠቀሰው የማኅበረሰቡ የነውር እሳቤ በውርስ ጊዜ ለሥርዓተፆታዊ ምድብ የማይፈቀዱ ዕደጥበባትን መውረስ ወይም መካፈል ነው። በሰሜን አቸፈር ማኅበረሰብ ወላጆች ሲሞቱና ልጆች የወላጆቻቸውን ንብረት በሚከፋፈሉበት ጊዜ አንዳንድ ዕደጥበባት ሥርዓተፆታን መሠረት ያደረጉና ከክፍፍል ውጪ ሆነው ለአንደኛው ለሚመለከተው ፆታ እንዲሰጥ የሚደረግበት ልማድ እንዳለ ማወቅ ተችሏል። ይኸውም የሟቾች ልጆች ወንድና ሴት ከሆኑ የወንድ ዕቃ ተብለው የተለዩት ወንዶች ልጆች እንዲወስዱ፣ የሴት ዕቃ ተብለው የተለዩትን ደግሞ ያለ ወንዶች ጣልቃ ገብነት ሴቶች ብቻ እንዲወስዱ የሚደረግበት ሲሆን ሴት ልጅ እያለች አገልግልን ወንድ ልጅ የእናቴ ንብረት ነው ብሎ መውሰድ አይችልም፤ ከጠየቀም እንደ ነውር ይቆጠራል። በአንጻሩ ወንድ ልጅ እያለ ሴት ልጅ የአባቷን እርፍና ቀንበር ይገባኛል ብላ አትጠይቅም። እነዚህ ቁሶች ከንብረት ክፍፍል/ውርስ ውጪ ፆታን መሠረት ባደረገ ከላይ ተነስተው የሚሰጡ መሆናቸውን ገልጸዋል (ወ/ሮ ውባለም አማረ፣ ቃ.መ. 15/02/2015ዓ.ም፣ ይስማላ ቀበሌ)። አንደውም ባልና ሚስት ወንድ ልጆች ብቻ ከወለዱ ሚስት "አገልግሌን የምታነሳ ሴት አጣቼ ልቀር" ማለቷ ወንዱም ሴቶች ብቻ ከሆኑ "ምነው እርፌን የሚጨብጥ ወንድ ተነፈገኝ" ሲሉ መደመጣቸው የተለመደ እንደሆነ ይናገራሉ።

### 4.3. ነውሮችን የማወጅ ወይም የመደንገግ ማኅበረሰባዊ ምክንያትና ሚና

እስካሁን በቀረቡት ተናጠላዊ ርዕሶች የዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም አውድ ውስጥ የታዩ የነውር እሳቤዎች ማኅበረሰቡ የፈጠረበትን አመክንዮ በግልጽ ከቀረበው ድንጋጌ ጀርባ ያለውን ኅቡኣዊ ተግባር በተመለከተ ትንታኔዎች ቀርበዋል። እንደ አጠቃላይ በተጠኚው ማኅበረሰብ የዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዓውድ ውስጥ የታዩ የነውር እሳቤዎች የመፈጠራቸው ወይም የመደንገጋቸው መንስኤ ማኅበረሰቡ እንደ ማኅበረሰብ እንዲቀጥል አንዳች ፋይዳ ይሰጡኛል፤ ኑሮዬን/ሕይወቴን ያቀኑልኛል፣ ከክፉ ነገር ይጠብቁኛል ከሚል እምነት የመነጨ ነው። በመሆኑም ከተሰበሰቡት መረጃዎች ነውሮችን ማወጅና ከእነሱ መከልከል ማኅበራዊና ሥነልቦናዊ መረጋጋትን በመፍጠር በኩል ሚና አላቸው ተብሎ እንደሚታሰብ ከመረጃዎች ማየት ተችሏል።

እንደ ማኅበረሰቡ ምልከታ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ለእነሡ ፆታዊ እሳቤ የተገቡ ዕደጥበባትን አለማዘጋጀታቸው እንደነውር የሚቆጠርበት ትልቁ ምክንያት ቁሶችን ማዘጋጀት በቁሶች ከመገልገል ባለፈ ሰላማዊና ጤናማ ማኅበረሰባዊ አኗኗርን ይፈጥራሉ፤ በተለይ ሴቷ ቤቷና ሥራዋ ላይ አተኩራ፤ ከወሬና አሉባልታ ርቃ ባሏንም ቤተሰቧንም አስከብራ የምትኖርበት የቁጥጥር ሥርዓትን ይዘረጋል ብለው ስለሚያምኑ ነው። በመሆኑም ከዚህ ሥርዓት በማፈንገጥ ዕደጥበባትን ከማዘጋጀት የሚሸሹት ከአውታታነትና ከሥንፍና ጋር የተገናኙ ስድቦችና ውግዘቶች ይደርስባቸዋል፤ በማኅበረሰቡ ዐይንም ዝቅ ያለ ምልከታ ይሰጣቸዋል። ለአብነትም የሚከተለውን ሥነቃል መመልከት የተሻለ መረጃ ይሰጣል።

እንዝርቱ ከማገር ጥጡ ከጉሽጉሻ
እሷስ የምትውለው ጡንጡን እንደውሻ

(አቶ መንበር፣ ቃ.መ. 10/11/2014ዓ.ም፣ ይብሊተረፊት ቀበሌ)።

ይህ ሥነቃል ሴቶች የማይሰፉና የማይፈትሉ ከሆነ፤ ሲያገቡ ከእናት የተበረከተላቸውን እንዝርትና ወስፌ ትተው መንደር ለመንደር ሲዞሩና አሉባልታ ሲቃርሙ ይውላሉ፤ ይህ ደግሞ የቤታቸውን ጉድለትና ሙላት በቅርቡ እንዲከታተሉ ስለማያደርጋቸው ቤታቸውን በአግባቡ መምራት እንዲሳናቸው እንደሚያደርጋቸው የቀረቡት ስንኞች አመላክተዋል። በመሆኑም ሴት ልጅ በተለይም በማኅበረሰቡ ልማድ የስፌትና የፈትል ወቅት ተብለው በተደነገጉት ጊዜያት ከመስፋትና ከመፍተል ቦዝና እንድትቀመጥ አይፈቀድላትም፤ ይህን ከተላለፈች ትነወራለች። በአጠቃላይ በማኅበረሰቡ እሳቤ ሴት ልጅ ቤቴን ቤቴን የምትል፤ ለሥራዋ፣ ለአመጋገቧ፣ ለአዋዋሏ ለከት ያላት እንጂ መርን የለቀቀች መሆን የለባትም ተብሎ ስለሚታመን ከዚህ ያፈነገጠች ብትኖር የሴትነት ልኬታዋን እንዲህ አቅሎ በሚያሳይ ሥነቃል እንደምትሸነቆጥ ያመለክታል። እግር ማብዛት የሴትነት ወግን ያስረሳል፤ ሥለዚህ ለዚህ ልጓሙ ደግሞ በሴት ደንብ ቁጭ ብሎ መስፋትና መፍተል ነው ብለው ያስባሉ። ይህም የመዋቅራዊ ጠቀሜታዊነት ንድፈሃሳብ አራማጆች በማኅበረሰቡ ልማድ የሚከወኑ ፎክሎራዊ ክዋኔዎችና ሥርዓቶች ያ ማኅበረሰብ ለተገነባበት መዋቅራዊ ትስስሮሽ አንዳች ፋይዳ የሚያበረክት መስሎ ሲሰማቸው በኑሮ ቅብብሎሽ ቀጣይነት እያገኘ እንዲሄድ ይፈልጋሉ። ለቀጣይነቱ እውን መሆን ደግሞ ማኅበራዊ ሕግና ሥርዓት፣ ነውርና ገደብ/ክልከላ በመሥራት ቁጥጥር ያደርጋሉ ከሚለው ጋር ይያያዛል። ዕደጥበባትን በማዘጋጀትና በመጠቀም ዐውድ ውስጥ ያለው የነውር እሳቤና ትዳርን ብሎም ቤተሰባዊ ክብርን በማስጠበቅ መካከል ያለው ትስስርም በዚህ መስመር ውስጥ የተቃኘ እንደሆነ የሚጠቁም ሁነት አለ። በመሆኑም በጥናቱ የታዩ የዕደጥበባት አዘገጃጀትና አጠቃቀም ክልከላዎች ወይም የነውር እወጃዎች የመፈጠራቸው ምክንያት የተረጋጋና የሰመረ ትዳር እንዲኖር በማድረግ በኩል እንዲሁም ማኅበራዊ መዋቅርና ስምምነትን የማስጠበቅ ሚና አላቸው ተብሎ እንደሚታሰብ ታውቋል።

ከመስክ በተገኙት የጥናቱ መረጃዎች መሠረት ከዕደጥበባቱ ዝግጅትና አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የተፈጠሩት ነውሮች ለተጠኚው ማኅበረሰብ ሥነልቦናዊ መረጋጋትን የሚፈጥሩና ማኅበረሰቡ አንዳች ክፉ ነገር ያመጣብኛል ብሎ ከሚፈራው ሁነት ይከልሉኛል ብሎ የሚያስባቸው ናቸው። ለዚህም መሠረቱ የማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት እንደሆነ ታይቷል። ለአብነትም ከገድና ከበረከት ጋር የተያያዙ ነውሮች እንዲሁም ከክፉ ዐይን ተጋላጭነት ጋር የተያያዙት ነውሮች እነሱን ብተላለፍ ለአንዳች ክፉ መንፈስ ተላልፌ እሰጣለሁ ከሚል ሥነልቦናዊ እምነትና ፍርሃት ጋር የተያያዙ ናቸው። ስለሆነም ክልከላዎችን ወይም ነውሮችን መፍጠሩና ማወጁ ፍራቻውን በማራቅ ሥነልቦናዊ መረጋጋት ይሰጣሉ የሚል እምነት እንዳላቸው መረዳት ተችሏል። በተጨማሪም ማኅበረሰቡን ከአደጋ መጠበቅ ያስችላሉ ተብሎ ይታሰባል።

### 4.4. የነውር ጥሰቶችን በተመለከተ የሚሰነዘሩ ማኅበረባህላዊ አጸፋዎች/ቅጣቶች

በተጠኘው ማኅበረሰብ የዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ የተጠቀሱትን ዐይነት ነውሮች ጥሶ የተገኘ ሰው በማኅበረሰቡ የተደነገጉ ቅጣቶችን እንዲቀበል የሚደረግበት አግባብ እንዳለ መረጃዎች አሳይተዋል። እኒህ ቅጣቶችም ለመጥፎ ነገሮች ተላልፎ መሰጠት፣ ትችትና ውግዘት እንዲሁም ፍቺ እንደሆኑ ታውቋል። ለአብነትም በነውር ዓይነቶች ትንተና ለመጠቆም እንደተሞከረው በሰርግ ቀን የሙሽራ ደንብ ዕቃዎችን አለመውሰድ፣ በፍቺ ጊዜ ቀምቶ ማስቀረትና በውርስ ጊዜ ለሥርዓተፆታቸው የማይገቡ ዕደጥበባትን መውረስ/መካፈል በማበረሰቡ ውስጥ ለትችት የሚዳርጉ እና ክብራቸውንም በማጉደፍ በማንኛውም ማኅበራዊ ግንኙነት ከእነሱ ጋር ላለመወዳጀት መፈለግ ዓይነት ማኅበራዊ አጸፋዎች ይደርስባቸዋል።

ለመጥፎ ነገሮች ተላልፎ መሰጠት በማኅበረሰቡ የዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዓውድ ውስጥ በተለይም በምጥ ጊዜ የሴት ዕቃዎችን ከድኖ ማስቀመጥ፣ ወንድ ልጅ ከጎታ እንዲገባ ማድረግ፣ ሴቷም ማጀቷ ውስጥ ያሉ የሴት ዕቃዎችን በምትከፋፍትበት ወቅት ድምጽ እላፊ ማውራት ከሴት ቆሌዋ ጋር መጣላትን ስለሚያመጣ ገድንና በረከትን በማራቅ ትቀጣቸዋለች ተብሎ ይታመናል። ከዚህ በተጨማሪም የሸክላ ቁሶች በሚሠሩበት ወቅት ጫጫታና ዐይን ማብዛት፣ ያለጉዝጉዞና ያለ ጌጣጌጥ መሥራት፣ ጥላ/ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሞ መሥራት በሸክላው ላይ ያለውን ቲሸት/ውቃቢ ስለሚያጎድፉና ስለሚያሳዝኑ ቁሶች ተሠርተው በሚደርቁበትና በሚተኮሱበት ጊዜ እንዲፈርሱ በማድረግ እንዲሁም የገበያ ገድ እንዲያጡ በማድረግ ሊቀጣቸው እንደሚችል የተሰበሰቡት መረጃዎች አመላክተዋል። በሌላ በኩል ውጥን ስፌቶችን መሸከም፣ ወስፌ ሰክቶ መተውና እግር በሚበዛበት ቦታ ተቀምጦ መስፋት ደግሞ ሰፊታዋን በገደቢስነት፣ በህመምና በሞት እስከመቅጣት ሊያደርሳት እንደሚችል መረጃዎች አሳይተዋል።

ሌላኛው ለነውር ጥሰት የሚሰነዘረው ማኅበራዊ ቅጣት ፍቺ እንደሆነ ታይቷል። በተጠኘው ማኅበረሰብ ልማድ ውስጥ ሴት ልጅ ጎጆ መሥርታ ስትኖር የሴት ወግ የሆኑ ዕደጥበባትን መስፋትና ጥጥ መፍተል የሴትነት ግዴታዋ ተደርጎ ይቆጠራል። በተለይም ማኅበረሰቡ የስፌት ወቅት ብሎ በመደባቸው ከመስከረም እስከ ህዳር ባለው ጊዜ የስፌት ቁሶችን ከማዘጋጀት ርቃ ሥራ ፈትታ እንድትቀመጥ አይፈቀድላትም። ይህን ማድረግ ካልቻለች ግን ከመነወሯም ባለፈ ትዳሯን በፍች እንዲቋጭ የሚያደረስ ቅጣት እንደሚገጥማት መረጃ አቀባዮች ይገልጻሉ። ከስፌትና ከፈትል ጋር በተያያዘ ያላት ብልሃት ትዳሯን ለመጠበቅም ሆነ ለማፍረስ ተፅዕኖው የጎላ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። የማትሰፋና የማትፈትል ከሆነች ትነወራለች፤ ከዚህ ነውር ተላቃ በሴትነት ወግ የማትኖር ከሆነ፤ የማትሰፋና የማትፈትል ከሆነ ከባሏ ጋር በአንድ ጎጆ ሥር አቆራኝቶ የሚያኖራቸው የአብሮነት ገመድ እንደሌለ የሚገልጹ በርካታ ሥነቃሎችን ያቀርባሉ። ለአብነትም የሚከተለውን መመልከት እንችላለን፡-

> ግራምጣ ሰንጥቃ ያላራሰች ቆንጆ
> ስንደዶ አድርቃ ያልሰበዘች ቆንጆ
> እንዝርቱን አሹራ ያልፈተለች ቆንጆ
> እስከመቼ ልትኖር ይዛ የሰው ጎጆ፤

(አቶ መንበር፣ ቃ.መ.፣ 23/10/2014ዓ.ም፣ ይብሊ ተረፊት ቀበሌ)።

በዚህ ቃልግጥም በማኅበረሰቡ ሴት ልጅ ከስፌትና ከፈትል ሙያ ርቃ እንድትኖር የማይፈቀድላት ወይም የምትከለከል እንደሆነ ነው። መሥፋትና መፍተል ጎጆ ቀልሶ ለመኖርና በትዳር ሕይወት ውስጥ ለመቀጠል ለሴቷ ዋስትና ተደርገው የሚቆጠሩ እንደሆኑ የተጠቆመና ይህን ካለደረገች ግን ትዳሯን ሊያስፈታት እንደሚችል በአራትኛው ስንኝ ላይ "እስከ መቼ ልትኖር ይዛ የሰው ጎጆ" ተብሎ የተገለጸው ሃሳብ ሳትሰፊና ሳትፈትይ በባለትዳ ማዕረግ እንድትኖር የሚፈቅድላት ማኅበረ ባህላዊ ሕግ እንደሌለና ሙያ አልቦ መኖር እንደምትከለከል ያመለክታል። በመሆኑም በተጠኘው ማኅበረሰብ ማኅበራዊ መዋቅር ውስጥ መስፋትና መፍተል በሴትነት ሚዛንና ክብር ልክ ለመገኘት፤ በትዳር ሕይወት የመኖርና የህልውና ጉዳይ ተደርጎ የሚቆጠር መሆኑን ማየት ተችሏል። ካልፈተለች ካልሰፋች ለትዳሯ ብቁ አይደለችም ተብሎ ይታሰባል። ታዲያ ይህ ማኅበረሰቡ የሰጣት የሴትነት ልኬታዋ ካለችበት ደረጃ ሊያወርዳት እንደሚችልና ያ ቦታ ለሌላ ለሚገባው ሰው ሊሰጥ እንደሚችል እንዲሁም ራሷን ለማስተካከል እድል እንዲኖራት የሚጠቁሙ፣ አያሻኝም ካለች ደግሞ የማይገባት ቦታ ላይ ስላለች ለሚገባውና ብቁ ለሆነ ሰው እንድትለቅ የሚነግሩ የሚከተሉት አይነት ቃልግጥሞች እንዳሉ መረጃዎች ጠቁመዋል።

የዘላን ጌሬራ ይመረጋል በበት
ያልቻልሽው ውጪና የቻለች ትግባበት።

(አቶ መንበር፣ቃ.መ.፣ ይብሊ ተረፊት ቀበሌ)

አቀማመጧ እንደጉሽጉሻ
አጎራረሷ እንዳዳኝ ውሻ
ያንንም ችሎ ባሏ ቢያኖራት
ጡዳ ተነስቶ ጥጥ አባራራት፤

(ወ/ሮ ሠራወርቅ፣ ቃመ. 09/02/2015ዓ.ም፣ ወንበርያ ባርካንታ ቀበሌ)።

ካልፈተለችና ካልሰፋች የሚታገሳት ሰው አይኖርም። ያስነውራታል፤ ከዚያም አልፎ እስከ ፍቺ የሚያደርስ ቅጣትም ሊያሰጣት እንደሚችል "የልቻልሽው ውጪና የቻለች ትግባበት"፤ "አገልግልሽን ይዘሽ ሂጂ ወደቤትሽ" የሚሉት በመጀመሪያውና በኹለተኛው ቃልግጥሞች የቀረቡት ስንኞች ያመላክታሉ። ጡዳ የዚህ ጥናት ተተኳሪ ከሆኑት ቀበሌዎች መካከል አንዱ ሲሆን የጥጥ አገር ነው። ከሦስተኛው ቃልግጥም እንደምንረዳውም በሌላው ሥራዋና በስንፍናዋ ባሏ ችሏት ቢኖርም በፈትል ግን መስማማት አልቻለምና "ጡዳ ተነስቶ ጥጥ አባረራት" የሚለው አራተኛው ስንኝ ይጠቁማል።

ለነውሮች ጥሰት የሚሰነዘር ሌላኛው ማኅበረሰባዊ ቅጣት ከክብር ዝቅ ማለት/ሹመት ሽልማትን ማጣት ነው። ሴት ልጅ እናቷ ቤት ሆናም ሆነ አማቷ ቤት እንድትሰፋና እንድትፈትል በማድረግ ችሎታዋ እንደሚመዘነው ሁሉ ወንድ ልጅም አማቶቹ ቤት ሲሄድ ሰሌን፣ መጥረጊያ እንዲሠራ፤ ቱቻ ገመድ እንዲፈትል፤ ገሳና የእርሻ ዕቃዎችን እንዲያዘጋጅ ይደረጋል፤ የአዘገጃጀት ዕውቀቱና

ብቃቱ ታይቶም ከአማቶቹ በኩል የተለያዩ አጸፋዎች ይሰነዘራሉ። እነዚህ አጸፋዎችም ምንአልባትም ክብሩን ከፍ የሚያደርጉ፣ ሹመት ሽልማት የሚያስቸሩ አሊያም የሚያስነጥቁ ይሆናሉ። ይህን አስመልክቶም አቶ ደመቀ የተባሉ መረጃ አቀባይ የተናገሩት ገጠመኛዊ ታሪክ እንደሚከተለው ቀርቧል።

> አንድ ጊዜ ፊታውራሪ ደምለው ሚባሉ የልጅ ባሎቻቸውን ለመስቀል በዓል ይጠሩና ለእያንዳንዳቸው አንድ አንድ ቋጠሮ ቱቻ[30] ሳር ተሰጧቸው ሲፈትሉ ከልጅ ባሎች መካከል አንደኛው በነፍጠኝነት በሁሉም ትልቅ ተጠሪ ነው፤ ግን ቱቻውን መፍተል አቃተው። ከያዘው ሁሉሥራ ይህን ሳይበልጥ ቀረ ተብሎ ምን ትልቅ ሆነ ገና ልጅ ነው ብለው "ልጅ በለው" ተብሎ ተጠራ፤ ልጅ ነው ገና አልለመደም ተብሎ እኮ ነው። በመስቀል የልጅ ባል ተጠርቶ ቁርስ እስከሚዘጋጅ ድረስ ወጥተው አንድ ቦታ ላይ ይቀመጣሉ ከዛ ላይ በሌላው ሥራ ከሌሎች የልጅ ባል በላይ ሆኖ ሳለ በቱቻ ፈተላው ግን ስላላለፈ "ልጅ በለው" ተብሎ ቀረ። ፈትሎ ቢሆን እንደ አቶ፣ እንደግራማችና ቀኝ አማች የሆነ ጀብዶ ሚሰጠው ነበር። አቶ በለው ተገኘ ተብሎ ሚጠራ የነበረው ሰውየ "ልጅ በለው" ተብሎ ቀረ(ቃ.መ. 06/01/2015ዓ.ም፣ ይስማላ ቀበሌ)።

ከገጠመኛዊ ታሪኩ ዕደጥበባትን ማዘጋጀት ወንዶች በጦር ሜዳ በሚፈጽሙት ጀብዱ ከሚያገኙት ሹመትና ሽልማት ያልተናነሰ ክብር የሚያሰጥና የወንድነት ልህቀትን የሚያስገኝ ቢሆንም በአንጻሩ በሥራው ብቁ ሆኖ ያልተገኘ ሰው ደግሞ እንደሚነወርና እንደባለታሪኩ ይገባው የነበረው ክብር ተነፍጎት፤ የሞራልና የክብር ኪሳራ ደርሶበት የሚኖርበት አጋጣሚ ሊፈጠር እንደሚችል የሚጠቁም ነው።

## 5. መደምደሚያ

በሰሜን አቸፈር ወረዳ ማኅበረሰብ የዕደጥበባት ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ የተስተዋሉ ነውሮች መነሻቸው የማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነቶች እንደሆኑ መረጃዎች አሳይተዋል። ይኸውም እነዚህ ነውሮች ማኅበረሰቡ የአኗኗር ዘዬውን ለማዋቀር፣ በማኅበራዊ ደረጃና መስተጋብር ውስጥ የዘረጋውን ማኅበረሰባዊ ደንብና ስምምነት አስጠብቆ ለመኖር እንዲሁም ከአንዳች ክፉ ነገርና ቁጣ ለማምለጥ ሲል የፈጠራቸው ክልከላዎችና የኑሮ መመሪያዎች እንደሆኑ ጥናቱ አመላክቷል። ይኸም ማኅበረሰቡ ነውሮችን በመጠበቁ አገኛለሁ ብሎ ከሚያምነውና በአንጻሩ በመጣሱ ደግሞ ይደርስብኛል ብሎ ከሚያምነው ነገር አንጻር የሚታዩ ናቸው። ከዚህ የተነሳም የነውሮቹ ይዘት ከክብር ጋር የተያያዙ፣ ከበረከትና ከገድ ጋር የተያያዙ እንዲሁም ከክፉ ዐይን ተጋላጭነት ጋር የተያያዙ እንደሆኑ ከመስክ የተገኙት መረጃዎች አመላክተዋል።

[30] ገመድ ለመፍተል የሚያገለግል የሳር ዓይነት

ከዕደጥበባት ዝግጅት ጋር በተያያዘ ያለው የነውር እሳቤ ገጽታ የሙያ ለመዳ መስመርን መሠረት ያደረገና ይህ የማኅበራዊ ግንባታ ንድፈሃሳብ ማኅበረሰባዊ ሥሪትና የፎክ ቡድን መሠረት እንዳላቸው የገለጹትን ያመላከተ ሆነው ተገኝቷል። እንዲሁም በዝግጅት አውድ የታዩት ማኅበረሰባዊ የነውር ምልከታዎች የቁሶችን ጥራትና የባለሙያዎችን ደህንት ከማስጠበቂያነት አንጻር ግላዊያዊ ተግባር (manifest function) እንዲሁም ሥራን ከማቀላጠፍ፣ የሙያ ለመዳ መስመርን ከመዘርጋት፣ ጤናማና የተረጋጋ ማኅበረሰባዊ መዋቅርን ከመገንባትና ከማስረጽ አንጻር ከሚኖረው ኅቡኣዊ ፋይዳ (latent function) የመነጨ ማኅበረሰባዊ ዕውቀትን/ልማድን ከማመላከቱም በላይ ማኅበረሰቡ ለሥርዓተፆታ ያለውን እሳቤ ለማስረጽና መዋቅራዊ ሥሪቱን ለማስጠበቅ የፈጠራቸው የነውር እሳቤዎች እንደሆኑ መረጃዎች አመላከተዋል።

ከዕደጥበባት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የታዩ የነውር እሳቤዎች ወይም ክልከላዎች ከክልከላው ጀረባ ያለውን ኅቡኣዊ ተግባር ያያዙ ሆነው ተገኝተዋል። ማኅበረሰቡ በተለያዩ ሁነቶች በተለይም በሕይወት ዑደት ሽግግር ሥርዓቱ ውስጥ ያወጣቸውን ደንቦች ወይም ስምምነቶችን የሚያፈርሱ ነገሮች እንዳይፈጸሙ የሚከለክሉ፤ ሥርዓተፆታዊ እሳቤዎችንና ማኅበራዊ መዋቅሮችን የሚያጸኑ እንደሆኑ ታውቋል። በአጠቃላይ በማኅበረሰቡ የዕደጥበባ ዝግጅትና አጠቃቀም ዐውድ ውስጥ የታዩ የነውር እውኛዎች ከግላዊያዊ ፋይዳቸው ጀርባ ኅቡኣዊ ፋይዳ እንዳላቸው ጥናቱ አረጋግጧል።

# ዋቢ ጽሑፎች


ሞላ ጀንበሬ። (2009)። "የነውር እሳቤ በሊቦ ከምከም ወረዳ ማኅበረሰብ እምነት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረምረቃ መርኀግብር ለፒ.ኤች.ዲ ማሟያ የቀረበ።

ኪዳነወልድ ክፍሌ። (1948)። *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ።* አዲስአበባ፤ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል። (1993) ። *አማርኛ መዝገበቃላት*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ደስታ ተክለወልድ። (1962)። *ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት።* አዲስ አበባ፤ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት።

ፈቃደ አዘዘ። (1991)። *የስነ ቃል መምሪያ።* አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት።

*Attfield, J. (2000). Wild ThingsThe Material Culture of Everyday Life.* Oxford፡ New York.

Berger, P. and Luckman, N. (1966). *The Social Construction of Reality.* USA; New York.

Donald, M. and Hurcombe, L. (2000). (ed.). *Gender and Material Culture in Archaeological Perspective.* MaCmilan press Ltd.

Emmanuel, A. A. (2013). "Taboo and the Maintenance of Social order in the old Ondo Province, southwestern Nigeria". *An International Multidisciplinary Journal, Etthiopia Vol. 7 (1), Serial No. 28, January, 2013:95-109.*

Fershtman, C., Uri, J., and Moshe, H. (2008). "Taboos and Identity: Considering the Unthinkabel". *American Economic Journal*: Microeconomics 3.2.139.

Freud, S. (1919). *Totem and Taboo Resemblances between the Psychic Lives of Savages and Neurotics*. Translated by Brill, A. London, George Routledge& Sons LIMITED.

Gennep, A. (1960). *The rites of passage*. Translated by Monika B. Vizledam and Gabbrielle L. Caffee London, Routledge and Kegan PAUL

Glassie, Henry. (1999*). Material Culture*. Bloomington and Indianpolis; Indiana University Press.

Hadush, G., Amha, K., Fereweini, G., Kidanmaryam, B., Alem, G., and Gberetsadikan, G. (2022). "Food Taboos and theire Perceived reasons among Pregnant Women in Ethiopia: a systematic Review". *BMC Pregnancy and Childbirth*, https://doi.org/10.1186/s12884-023-05437-4.

Hardin, K.L. (1996). *Technological style and the making of culture three Kono context of production. In African material culture*. Arnoldi,M.J., Geary, C.M., Hardin, K.L.(ed.). Bloomington and Indianapolis; Indian Univerity Press.

Katan, D. (1999). *Translating Cultures, An Introduction for Translators, Interpreters and Mediators*. Manchester: St. Jerome Publishing.

McNamara, K., and Wood, E. (2019). "Food Taboos, Health belief, and gender: understanding household food choice and nutration in rural Talkistan". *Journal of Health, Population and Nutrition* (2019)38:17 https://doi.org/10.1186/s41043-019-0170-8

Merton, R. (1968). *Social Theory and Social Structure.* New York, Free Press.

Motz, Marilyn. (1998). "The practice of belief." Journal of American Folklore. Vol 111 NO 441. 339-355.

Omobola, Odejobi. (2013). "An overview of taboo and superstition among The Yourba of Soutwest of Nigeria". *Mediteranean Journal of Social Science* Vol 4 No 2 2039-2117.

Osei, J. (2006). "The Value of African Taboos for Biodiversity and Sustainable Development". *Journal of Sustainable Development in Africa* 8.3 (2006): 42-61.

Radcliffe, B. (1952). *Structure and function in primitive society Essays and Addresses* Printed in Great Britain at the University Press Aberdeen.

Ramulondi, M., Wet, H. D. and Ntuli, N. R. (2021). "Traditional Food Taboos and Practices during Pregnancy, Postpartume recovery, and infant care of Zulu women in northern Kwa Zulu-Natal". *Journal of Ethnobiology and Ethnomedicine*. https:/doi.org/10.1186/s13002-021-00451-2.

Sharma, A., Thuker, D., and Uniyal, SK. (2020). "Taboo: Traditional belief and Custom for Resource Management in the Western Himalaya". *Indian Journal of Traditional Knowledge*. Vol 20(2), April 2021, pp 557-581.

Tylor, E. (1871). *Primitive Culture: Researces into the Development of Mythology, Philosophy, Religion, Art, and Custom.* London, John Murray, Albemarle Street.

Zaro, M. (2024). "Clarifying Key Concerns about the Dating of Holy Relics: The Holy Chalice of the Last Supper at the Cathedral of Valencia". *Hertiage* vol 7, 139 -161, https://doi.org/10.3390/heritage7010007.